
# አማርኛ

## እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ



**ስምንተኛ (፰ኛ) ክፍል**

በአዲስ አበባ ት/ቢሮ ተዘጋጅቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ እና በዲላ መምህራን ት/ኮሌጅ የተስማማ

# አማርኛ

## እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

አስማሚዎች፡-

ቴዎድሮስ ቦጋለ (MA)

ሀብታሙ መስፍን (M.ED)

እስከዳር ገበያው (MA)

አርታኢ፡-

ፍቅርተ መኮንን (MA)

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እና
በዲላ ትምህርት ኮሌጅ የቴክኒክ ድጋፍ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል፡፡

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው፡፡

## ማውጫ ገፅ


ምዕራፍ አንድ.....1
የሥራ ሥነ ምግባር.....1
ምዕራፍ ሁለት.....13
ባህላዊ ቅርስ.....13
ምዕራፍ ሶስት.....26
ሰብዓዊ እሴቶች.....26
ምዕራፍ አራት.....38
አጭር ልቦለድ.....39
ምዕራፍ አምስት.....54
የሕዝብ ብዛት.....55
ምዕራፍ ስድስት.....68
በረሃማነት.....68
ምዕራፍ ስምንት.....97
ሰላም.....97
ምዕራፍ ዘጠኝ.....119
የአየር ንብረት ለውጥ.....119
ምዕራፍ አስር.....136
ተውኔት.....136

## መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያና ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄደው የ8ኛ ክፍል የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ አማርኛን በመጀመሪያ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ፤ በተጨማሪም የቃላትና የሠዋስው እውቀት እንዲገኙ ለማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት አካል ነው።

የመምህር መምሪያው በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ በመመሥረት በአዳዲሶቹ የመማሪያ-ማስተማሪያ መሣሪያዎች ውስጥ በጥቅም ላይ ስለዋሉት የማስተማር አቀራረቦችና ስለአዲሱ መርሃትምህርት (ሥርዓተ ትምህርት) መነሻ ሀሳቦች መሠረታዊ መረጃ ይሰጣል። በአንድ ምዕራፍ ሥርም ለቀረቡት የትምህርት ይዘቶች ግልጽ መመሪያ ያቀርባል። በተጨማሪም ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ለመከታተልና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ተገቢውን ድጋፍና ማጠናከሪያ ለመስጠት ተከታታይ ምዘናን መተግበር የሚቻልበትን መርሕ ይዟል። በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሥርዓተፆታንና የአካቶ ትምህርትን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚገባ ድጋፍ ይሰጣል።

በመጨረሻ ላይም ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጀው አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ) መርሃት ምህርት ተያይዟል። ይኸ መርሃ ትምህርትም በየደረጃው በእያንዳንዱ ወሰነ ትምህርት ተማሪዎች ሊያዳብሯቸው ስለሚገቡ የቋንቋ ብቃቶች ያሳያል።

## የማስተማር መርሆዎች

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በሁሉም ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) እንዲሁም ቃላትና ሰዋስው የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች የማንበብንና የመጻፍን ችሎታዎች በሚያዳብሩበት መልክ ተደራጅተዋል፡፡

አዳምጦ/ አንብቦ መረዳት የሚዳብረው በቅድመ ማዳመጥ/ ማንበብ፣ በማዳመጥ/ በማንበብ ሂደትና በድኅረ ማዳመጥ/ ማንበብ ተግባራት ነው፡፡ ተማሪዎች ስለጽሑፉ (በቅድመ ማዳመጥ/ ማንበብና በማዳመጥ/ በማንበብ ሂደት ወቅት) እንዴት መገመት እንደሚችሉ፣ መረዳታቸውን በራሳቸው እንዴት መቆጣጠር እንደሚችሉና ያዳመጡትን ወይም ያነበቡትን እንዴት መገምገም እንደሚችሉ መማር አለባቸው፡፡

መናገርና መጻፍ በተገቢ ሁኔታ ራስን መግለጽን ይመለከታል፡፡ ይኸውም ቋንቋውን በትክክል መጠቀምንና ሀሳብን ለሌላ አካል በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በግልጽ ማስተላለፍን ይጨምራል፡፡ በመሆኑም የንግግርና የጽሑፍ ክሂል የሚዳብረው ተማሪዎች በተቻለ መጠን ራሳቸውን እንዲገልጹ በርካታ ዕድሎች ሲመቻቹላቸውና ወቅታዊ ግብረመልሶችም ሲያገኙ ነው፡፡

የቃላት ዕውቀት፣ ቃላትን የመለየት/ የመረዳትና ፍቻቸውን የመገንዘብ ችሎታ ነው፡፡ የተገደበ የቃላት ዕውቀት ያላቸው ተማሪዎች የሚያነቡትንም ሆነ የሚያዳምጡትን ጽሁፍ መልእክት ለመረዳት የቃላት እውቀት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የቃላት ዕውቀት የሚዳብረው አዳዲስ ቃላትን ከነፍቻቸው በማስተማር፣ ተማሪዎች እነዚህን ቃላት በንግግርም ሆነ በጽሑፍ እንዲጠቀሙባቸው በማበረታታትና ከሚያነቡት ወይም ከሚያዳምጡት ጽሑፍ ውስጥ የቃላትን ፍቺ የሚያገኙበትን ብልሃት (ስትራተጂ) በማስተማር ነው፡፡

ሰዋስው፡- በመርሃ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ ለደረጃው በተዘጋጀው የትምህርት ወሰንና ተለጣጥቆ መሠረት የተለያዩ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በመማርና በትክክል በመጠቀም ላይ ያተኩራል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የዘረዘርናቸው የትምህርት ይዘቶች ማዕከል ያደረጉት በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ዓላማዎች ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ
# የሥራ ሥነ ምግባር

**(ክፍለ ጊዜ 9)**

***የምዕራፉ አላማዎች፡-*** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- በጥሞና አዳምጠው በተነገረበት አውድ መሰረት ይመልሳሉ፤
- የስራ ስነ ምግባርን ጽንሰ ሃሳብ ይገልጻሉ፤
- አዳዲስ ሀሳቦችን አካተው ጽሁፍ ይጽፋሉ፤
- የስራ ስነ ምግባር አመላካች ነገሮችን ይገልጻሉ፤
- የቋንቋውን ትክክለኛ የሰዋሰው አወቃቀር ይጠቀማሉ፡፡

***የምዕራፉ ይዘቶች፡-***

- የሌሎችን ሀሳብ ማዳመጥ
- ቋንቋን በተለያየ አውድ ውስጥ መጠቀም
- የለሆሳስ ንባብ
- ዕህፈት
- ተዘውታሪ ቃላት
- የቋንቋ መዋቅር

**ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ**

**ሰው ለስራ**

**የትምህርቱ አቀራረብ፡**

**ቅድመ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

«ሰው ለስራ» የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎችዎ ከማንበብዎ በፊት፡-

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- ምንባቡን በዝግታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- እየተከታተሉዎት መሆናቸውን ለማረጋገጥ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡
- በትኩረት እንዲከታተሉዎት ምክር ይለግሷቸው፡፡

- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸውም ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርሶ መሪነት በቃላቸው እንዲሰሩ ያድረጓቸው፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡

**ምዘና**

- ካዳመጡት ምንባብ ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- ሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ ማድረጋቸውን መቃኘት፤
- የንግግር ክሂላቸውን ማጎልበት እንደቻሉ መገምገም፤

**መርጃ መሳሪያ**

- መቅረፀ ድምፅ

## ሰው ለስራ

ሰው የተፈጠረው በስራና ለስራ መሆኑን በመገንዘብ በምድር ላይ ሲኖር ራሱ በፈጠረውም ሆነ ሌሎች በፈጠሯቸው የስራ መስኮች ላይ ተሰማርቶ ኑሮውን ማሻሻልና ራሱን መቀየር ይኖርበታል፡፡ በስራ አለም ሲኖር ደግሞ ምንድን ነው የምሰራው? ለምን አላማ ነው የምሰራው? የማገኘው ውጤትስ ምንድን ነው? ለሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ከራሱ ማግኘት ይጠበቅበታል፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ከራሱ የሚያገኝ ከሆነ ደግሞ የሚሰራው ስራ ጥፋት እንዳያስከትል፣ ጉዳት እንዳያመጣ፣ ሌሎችን እንዳይረብሽና የሰሩትን ስራ እንዳበላሽ ማድረግ ይችላል፡፡

የሰው ልጅ ሁልጊዜ አዲስ ነገርን የሚሻ ስለሆነም የሚሰራውን ስራ በጊዜ ሂደት እያስተካከለና እያረመ ይሄዳል፡፡ ንጹህ አዕምሮ ያለው ሰው ዛሬ ላይ የሰራውን ስህተት ነገ ላይ አይደግመውም፡፡ የስኬታማ ስራና ሀብት ፈጠራ ጥበበኞች እንደሚናገሩትም አንድ ጠንካራ ሰው ስራና ውጤቱን ራሱ ካልገደበው በስተቀር ለአንዱ ትልቅ ለሌላው ደግሞ ተቆንጥሮ በትንሹ የተሰጠው አይደለም፡፡ ከበርካታ የስኬታማነት ልምዶች በግልጽ ማየት እንደሚቻለው መደህየትም ሆነ መበልጸግ፣ መስነፍም ሆነ መትጋት፣ መማርም ሆነ አለመማር፣ ክፉም ሆነ ደግ መሆን፣ ማደግም ሆነ አለማደግ፣ ማትረፍረፍም ሆነ ማብቃቃት በአብዛኛው የግል ምርጫዎችና ውሳኔዎች ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ ማሰብ ለራስ መልካም ወዳጅ የመሆን ቁልፉ መሳሪያ ነው፡፡ ሰው ለራሱ መልካም ወዳጅ ሲሆን ለትልቅ ስኬት ይበቃል፡፡ ምክንያቱም ለራሱ የልብ ወዳጅ ከሆነ ለስራና ለእድገት የተሰጠውን ማንነት አያባክነውም፡፡

**መምህር!**

ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ እየተከታተሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሾቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

- ❖ ካዳመጣችሁት ምንባብ በመነሳት በስራና በሰው መካከል ስላለው ተጠየቃዊ ግንኙነትን ምን ተረዳችሁ?
- ❖ ሰው በስራ ዓለም ሲኖር ምን ምን ነገሮችን ማሰብ ይኖርበታል?

ስራን መስራት የተለመደና ያለ ቢሆንም ሰዎች ሲሰሩ ማሰብ ያለባቸው ነገሮች እንዳሉ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ሰው የሚሰራውን ስራ መውደድና በስራው ውጤታማ እንደሚሆን አውቆ መስራት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ስራዎች የሚበደሉትና በአግባቡ የማይሰሩት ሰዎች ለስራቸው ፍቅር ስለሌላቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ስራቸውን በሚፈለገው መጠን አድምተው እንዳይሰሩ ያደርጋቸዋል፡፡ እውነታው ግን ሰዎች በተለያየ ምክንያት የማይወዱት የስራ መስክ ላይ እንኳ ቢሰማሩ የተሰጣቸውን ስራና ሀላፊነት በጥንቃቄ መወጣት ነው፡፡ ጥንቃቄ ሰንል ለስራው፣ ለሰራተኞች፣ ለምንሰራበት ቁሳቁስ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

ሌላው ስራን ስንሰራ ማድረግ ያለብን ነገር በዕውቀት ላይ ተመስርቶ መስራት ነው፡፡ ሰዎች የሚሰሩትን ስራ በዕውቀት ላይ ተመስርተው የሚሰሩ ከሆነ ውጤታማ መሆናቸው አያጠራጥርም፡፡ እውቀትን ደግሞ በሁለት መንገድ ልናገኘው እንችላለን፡፡ አንድም በትምህርት አንድም በልምድ፡፡ እነዚህን ነገሮች ተጠቅመን ስራችንን በዕውቀት ማከናወን ይኖርብናል፡፡

በመጨረሻም ሰዎች ከፈጣሪ የተሰጣቸውን ጥበብና እውቀት ተጠቅመው ዓለምን የመቀየር አቅም እንዳላቸው አሁን ያለንበት የዓለም ነባራዊ ሁኔታ ምስክር ነው፡፡ በመሆኑም ስራን በመስራት ራስን፣ ቤተሰብን፣ አካባቢን፣ ሀገርንና ዓለምን መቀየር ተገቢ ነው፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

**መምህር!**

በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች በቃል በማሰራት የተማሪዎቹን የአዳምጦ መረዳት ደረጃ ይፈትሹ፡፡ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

መምህር!


- በመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ውይይት ተደርጎባቸው የሚቀርቡ ስለሆኑ ተማሪዎቹን ሶስት ሶስት በማድረግ ያቧድኗቸው፡፡
- ቡድኑ ፆታዊ ስብጥር እንዲኖረው ያድርጉ፡፡
- በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ይዘዟቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- በጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡
- በየቡድናቸው እየሄዱም የግልፅነት ጥያቄ ካለ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- በመጨረሻም የተወያዩበትን ሀሳብ በተወካዮቻቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፤ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡
- መምህር እባክዎ የአካል ጉዳትና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች እንደየ ችሎታቸው እንዲሳተፉ ያድርጉ፡፡

**ምዘና**

- ቡድን መስርተው ለመወያየት መዘጋጀታቸውን መፈተሽ፤
- በተሰጧቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረጋቸውን መከታተል፤
- የአካል ጉዳትና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ መሆናቸውን መገምገም፡፡



## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ቅድመ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

መምህር!

- ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት መማሪያ መጽሐፉ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በማቅረብ በውይይት እንዲሳተፉና እንዲነቃቁ ያድርጉ፡፡
- በቅድሚያ ተማሪዎች ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸውና እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸውና የከንፈር እንቅስቃሴ እያዩ እንዲረዱ ያድርጉ፡፡

**ጊዜ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- ምንባቡን ተማሪዎች በአንቀፅ በአንቀፅ እየተከፋፈሉ በየተራ እንዲያነቡት ያድርጉ፡፡
- ንባቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ ምክንያታዊ ሆነው መልሳቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- አንብበው መረዳታቸውን ድህረ ንባብ ጥያቄዎችን በማሰራት መገምገም፤
- አካል ጉዳተኛና አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ በንቃት ተሳትፎ ማድረጋቸውን መፈተሽ፤

**መልመጃ አንድ፡-**

**ምንባቡን በሚገባ በማንበብ የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ ደግሞ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡**

፩. እውነት

፪. ሀሰት

፫. እውነት

፬. እውነት

፭. ሀሰት

**መልመጃ ሁለት፡-**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡**

| | |
|---|---|
| ፩. ለ | ፬. ሀ |
| ፪. ሐ | ፭. ሀ |
| ፫. መ | ፮. ሐ |

**ክፍል አራት፡- መጻፍ**

## የትምህርቱ አቀራረብ

**ትዕዛዝ አንድ**

መምህር!

- ተማሪዎቹ በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አስተካክለው እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

**ትዕዛዝ ሁለት፡-**

- በመጽሀፉ ላይ ተጀምሮ ያላለቀውን አንቀጽ ሀሳብ ሊያሟሉ የሚችሉ ዓረፍተ ነገሮችን ጨምረው እንዲያጠናቅቁ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክለው አንቀፅ መፃፋቸውን ማረጋገጥ፤
- በጅምር የቀረበውን አንቀፅ ሀሳቡን ጠብቀው መጨረሳቸውን መፈተሽ፤

መልመጃ አንድ፡-

የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተል በማስተካከል አንቀፅ ፃፉ፡፡

፩. ሐ

፪. ሀ

፫. ሠ

፬. መ

፭.ለ

ክፍል አምስት፡- ቃላት

መልመጃ ሁለት

ክፍል ሶስት በቀረበው ምንባብ መሰረት በ «ሀ» አምድ ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በ«ለ» ካሉት በመምረጥ አዛምዱ፡፡

፩. ሐ

፪. ሰ

፫. ረ

፬. መ

፭. ሸ

፮. ቀ

፯. ሠ

፰. ሀ

**ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው**

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር !**

- ✓ የቋንቋ መዋቅርን በተመለከተ በመማሪያ መፅሀፉ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በምሳሌ አስደግፈው መጠነኛ ገለፃም ያድርጉላቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- ✓ ተማሪዎች የመምህራንን የስራ ስነምግባር በተመለከተ መረጃ በመሰብሰብ የቋንቋውን ተገቢ መዋቅር ጠብቀው ድርሰት እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሁሉም ተማሪዎች መፃፍ እንደሚኖርባቸው ይንገሯቸው፡፡
- ✓ የፃፉትን አንቀፅ እርስ በዕረስ በመቀያየር እንዲተራረሙ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም እርስዎ እርማት ይስጧቸው፡፡ በቃልም ሆነ (ጎበዝ፣ በጣም ጎበዝ፣ በርታ፣ በርቺ ወዘተ) በሌላ በሚችሉት ነገር ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- የቋንቋ መዋቅርን በተመለከተ አጭር ማስታዎሻ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤
- የቋንቋን ተገቢ መዋቅር ጠብቀው ድርሰት መፃፋቸውን መፈተሽ፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች መፃፍ መቻላቸውን መገምገም፤

# ምዕራፍ ሁለት

# ባህላዊ ቅርስ

**(ክፍለ ጊዜ12)**

***የምዕራፉ አላማዎች፡-*** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የሌሎችን ሀሳብ በጥሞና ያዳምጣሉ፤
- የባህላዊ ቅርስን ምንነት ያብራራሉ፤
- ከምንባቡ የወጡ አዳዲስ ቃላትን ፍች ይሰጣሉ፤

***የምዕራፉ ይዘቶች፡-***

- ✓ በአትኩሮት ማዳመጥና መመለስ
- ✓ ውስብስብ ሁነቶችን መተረክ
- ✓ ማንበብና ዘገባ
- ✓ አከራካሪ ጽሑፍ
- ✓ አዳዲስ ቃላት
- ✓ የአሁን ጊዜ ግስ

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## ቅርሶች በኢትዮጵያ

## የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

«**ቅርሶች በኢትዮጵያ**» የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎችዎ ከማንበብዎ በፊት፡-

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- ምንባቡን በዝግታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- እየተከታተሉዎት መሆናቸውን ለማረጋገጥ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡
- በትኩረት እንዲከታተሉዎት ምክር ይለግሷቸው፡፡
- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸውም ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- ❖ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርሶ መሪነት በቃላቸው እንዲሰሩ ያድረጓቸው፡፡
- ❖ ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡
- ❖ ለሚሰጡት መልስ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- ካዳመጡት ምንባብ ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- ሁሉም ተማሪዎች የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን መስራት መቻላቸውን መቃኘት፤
- ለሚሰጡት ምላሽ ምክንያታዊ መሆናቸውን መዳሰስ፤

## ቅርሶች በኢትዮጵያ

ቅርስ የህዝቦች ማንነት የሚገለፅበትና የረጅም ዘመን ባህላቸውንና ታሪካቸውን እንዲገነዘቡ የሚረዳ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብት ነው፡፡ ከምንጩ አንጻር በአንድ በኩል በተፈጥሮ የታደልነውን ተፈጥሯዊ ቅርስ ሲመለከት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ካለፈው ትውልድ የወረስነውን ባህላዊና ታሪካዊ ሰው ሰራሽ የፈጠራ ውጤት የሚመለከት ነው፡፡ የቅርስ ቁሳዊና መንፈሳዊ ይዘት በቅድመ ታሪክና በታሪክ ዘመን የሰው ልጅ የፈጠራና የስራ እንቅስቃሴ ውጤት የሆነ፣ የተፈጥሮ የለውጥ ሂደትን የሚገልፅና የሚመሰክር በሳይንስ፣ በታሪክ፣ በባህል፣ በስነጥበብና በዕደጥበብ ይዘቱ ከፍተኛ ተፈላጊነት ዋጋ ያለው ማንኛውም ነገር ነው፡፡ የቀደምት አባቶችና እናቶች ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሰርተውና ተጠቅመውበት ትተውት ያለፉትና በዓይን ለመታየትና በጆሮ ለመሰማት የሚችል ሲሆን፣ የብሄር ብሄረሰቦችን ልዩ ልዩ ትርኢቶችና ተመሳሳይ የማህበረሰቡ ወግና ልማዶችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ በተጨማሪም የብሄራዊ ማንነት መለያ ማህተም በመሆን በኩል የላቀ አገልግሎት ያላቸውና መስዋዕትነትን ለመዘከር የቆሙ ሀውልቶች፣ ጠላት ድል የሆነባቸው ታሪካዊ ስፍራዎች፣ በጦርነት ጊዜ የተዜሙ ሽለላዎች፣ ግጥሞች፣ ድራማዎች ወዘተ. ሁሉ ይካተቱበታል፡፡

በአለም አቀፍ የቅርስ መዝገብ ውስጥ የተመዘገቡ የሀገራችን ቅርሶች የተባበሩት መንግስታት የዓለም የቱሪዝም ድርጅት በዓለም ቅርስነት ከመዘገባቸው ቅርሶች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር በመያዝ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ሀገራት ቀዳሚ ናት፡፡ ኢትዮጵያም ብዛት ያላቸውን ቅርሶች በተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት በዓለም አቀፍ ቅርስነት ያስመዘገበች ሲሆን ብሔራዊ ቤተ መዛግት እና ቤተ-መፃህፍት ኤጀንሲ ካሰባሰባቸው የመረጃ ሀብቶች መካከል 12 የስነ-ፅሁፍ ቅርሶች በዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገቡ አድርጋለች፡፡

***መምህር!***

***ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ እየተከታተሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሾቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡***

- ***ተማሪዎች! ቅርስን በተመለከተ እስካሁን ካዳመጣችሁት ምን ተረዳችሁ?***
- ***በዩኔስኮ የተመዘገቡ የኢትዮጵያ የሥነጽሑፍ ቅርሶች ምን ምን ይመስሏችኋል?***

በዩኔስኮ ከተመዘገቡ የስነ-ፅሁፍ ቅርሶች መካከል ስምንቱ በብራና የተፃፉ ሲሆኑ አጼ ቴዎድሮስ ለእንግሊዟ ንግስት ቪክቶሪያ የጻፉት ደብዳቤ፣ የሸዋው ንጉስ ሳህለ ስላሴ ለእንግሊዝ ንግስት የጻፉት ደብዳቤ፣ ዳግማዊ አጼ ሚኒሊክ ለሞስኮው ንጉስ ኒኮላስ ቄሳር 2ኛ የጻፉት ደብዳቤ እና የዳግማዊ አፄ ምኒልክ ታሪክም በዩኔስኮ ከተመዘገቡ የስነ-ፅሁፍ ቅርሶች ውስጥ ናቸው፡፡

ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ ከላይ ከጠቀስናቸው ቅርሶች ይበልጥ የሚታወቁ እና የሚዳሰሱ ቅርሶች በዩኔስኮ የቅርስ መዝገብ ላይ አስመዝግባለች፡፡ እነኝህ ቅርሶቻችንም፡- በአማራ ክልል የሚገኙት የላሊበላ ውቅር አቢያተ ክርስቲያናት፣ የጎንደር ነገስታት ቤተ-መንግስትና የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ በትግራይ ክልል የሚገኘው ጥንታዊ የአክሱም ሀውልት፣ በአፋር ክልል የሚገኘው የታችኛው አዋሽ ስምጥ ሸለቆ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል የሚገኘው የታችኛው ኦሞ ስምጥ ሸለቆ፣ የኮንሶ መልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ በደቡብ ክልል የሚገኘው የጢያ ትክል ድንጋይ እና በሐረሪ ክልል የሚገኘው የሐረር ጀጎል ግንብ ናቸው፡፡

የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶቻችን በጉርጎሮሳዊያኑ ዘመን አቆጣጠር በ2003 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ

ባፀደቀው የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርስ ጥበቃ ስምምነት መሰረት የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ ማለት ክብረ በዓላትን ጨምሮ ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህላቸው አድርገው የተቀበሏቸውን ድርጊቶች፣ እውቀቶች፣ ስነ-ጥበባት፣ ህግጋት፣ እምነቶች፣ ማህበራዊ ክንዋኔዎችና ስነ-ስርዓቶችን የሚያካትት ነው፡፡ በዚህ እረገድ የመስቀል በዓልንና የሲዳማ ዘመን መለወጫ የጨንበላላ በዓልን በዓለም የውክልና መዝገብ ውስጥ ማካተት ከመቻሉም በላይ የገዳ ስርዓት በ2009 ዓ.ም እና በ2012 ዓ.ም ደግሞ የጥምቀት በዓል  በዚሁ መዝገብ ውስጥ ለማካተት የተደረገው ጥረት ተሳክቶ ተመዝግበዋል፡፡

**(ከኢትዮጵያ ቱሪዝም መጽሐፍ እና ከቀድሞው የ11ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ላይ የተገኘን መረጃ በማሻሻል የተወሰደ)**

## ድህረ ማዳመጥ

**መምህር!**

በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች በጽሑፍ በማሰራት የተማሪዎቹን የአዳምጦ መረዳት ደረጃ ይፈትሹ፡፡

**መልመጃ አንድ፡-**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

፩. ሀሰት

፪. እውነት

፫. እውነት

፬. ሀሰት

፳. እውነት

**መልመጃ ሁለት**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተነበበላችሁን የማዳመጥ ምንባብ መሰረት ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

፩. ሐ ፬. ሀ

፪. ለ ፭. መ

፫. መ ፮. ለ

**ክፍል ሁለት፡- መናገር**

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- የመጀመሪያውና የሁለተኛው ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ውይይት ተደርጎባቸው የሚቀርቡ ስለሆኑ ተማሪዎቹን ጥንድ ጥንድ በማድረግ ያቧድኗቸው፡፡
- በተቻለ መጠን ሴትና ወንድ ያድርጓቸው፡፡
- በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ይዘዟቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- በጥያቄዎቹ ላይ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡
- በየቡድናቸው እየሄዱም የግልፅነት ጥያቄ ካለ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- በመጨረሻም የተወያዩበትን ሀሳብ በተወካዮቻቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፤ ማበረታታቸም

ያድርጉላቸው፡፡

- ሶስተኛው ጥያቄ ግን መረጃ መሰብሰብን ስለሚጠይቅ ተማሪዎቹ በቤት ስራ መልክ በፅሁፍ እንዲሰሩት ቢያድርጉ መልካም ነው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች የባህልና ቱሪዝም ባለሙያ ወይም ሌላ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ ሰርተው መምጣት እንደሚኖርባቸው ትዕዛዝ ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- ሴትና ወንድ ሆነው ለመወያየት መዘጋጀታቸውን መፈተሽ፤
- በተሰጧቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረጋቸውን መከታተል፤
- የተሰጣቸውን የቤት ስራ ባለሙያ ጠይቀው መስራት መቻላቸውን ማረጋገጥ

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

### የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት መማሪያ መጽሐፉ ላይ ያሉትን የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች በማቅረብ በውይይት እንዲሳተፉና እንዲነቃቁ ያድርጉ፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- ❖ ምንባቡን ተማሪዎች በአንቀፅ በአንቀፅ እየተከፋፈሉ በየተራ እንዲያነቡት ያድርጉ፡፡
- ❖ አያይዘውም ተማሪዎቹ ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ንብቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- ❖ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ ምክንያታዊ ሆነው መልሳቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- ❖ አንብበው መረዳታቸውን የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን በማሰራት መገምገም፤
- ❖ አካል ጉዳተኛና አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ በንቃት ተሳትፎ ማድረጋቸውን መፈተሽ፤

**ድህረ ንባብ**

**መልመጃ አንድ፡-**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ ደግሞ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡**

፩. እውነት

፪. እውነት

፫. ሀሰት

፬. እውነት

፭. ሀሰት

**መልመጃ ሁለት**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡**

፩. መ  ፪. መ  ፫. ለ

**ክፍል አራት፡- መጻፍ**

## የትምህርቱ አቀራረብ

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- አከራካሪ ድርሰትን በተመለከተ በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን አጭር ማስታወሻ እዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- አከራካሪ ድርሰት እንዴት እንደሚፃፍ ከቀረበው ምሳሌ በመነሳት ግልፅ ያድርጉላቸው፡፡
- «ባህላዊ ቅርሶችን የመጠበቅ ኃላፊነት ያለው መንግስት ወይስ እያንዳንዱ ግለሰብ? በሚል ርዕስ ባለ ሶስት አንቀፅ ድርሰት እንዲፅፉ ይዘዟቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች መፃፍ እንደሚኖርባቸው ይንገሯቸው፡፡
- የፃፉትን አንቀፅ ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡
- በመጨረሻም ግብረመልስም ይስጧቸው፤ ያበረታቷቸውም፡፡

**ምዘና**

- አከራካሪ ድርሰትን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤
- ባለሶስት አንቀፅ አከራካሪ ድርሰት መፃፋቸውን መዳሰስ፤
- ሁሉም ተማሪዎች ፅፈው መምጣታቸውን መፈተሸ፤
- የፃፉት ድርሰት አከራካሪ ድርሰት መሆኑን መገምገም፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

**መምህር!**

- ✓ ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከምንባቡ የወጡ ቃላትን አውዳዊ ፍች ተጠቅመው አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ በምሳሌ ያሳይዋቸው፡፡
- ✓ የቃላትን አውዳዊ ፍች ተጠቅመው  ዓረፍተነገር እንዲፅፉ ይዘዟቸው፡፡
- ✓ በተጨማሪም ቃላትን ከተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- የቃላትን አውዳዊ ፍቺ በመጠቀም አረፍተ ነገር መመስረታቸውን መፈተሽ፤
- ተመሳሳይ የሆኑ ቃላትን በትክክል ማዛመዳቸውን መገምገም፤

**መልመጃ ሁለት**

**በምንባቡ መሰረት በ «ሀ» አምድ ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በ«ለ» ካሉት በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| | |
|---|---|
| ፩. ሰ | ፭. ሸ |
| ፪. ረ | ፮. ለ |
| ፫. መ | ፯. ሀ |
| ፬. ሠ | ፰. ሐ |

**ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው**

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ✓ የሀላፊ ጊዜን በተመለከተ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጓቸው፤
- ✓ በምሳሌ አስደግፈው መጠነኛ ገለፃም ያድርጉላቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- ❖ ከቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የአሁን ጊዜ ግስን የያዙ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡
- ❖ በተጨማሪም የአሁን ጊዜ ግሶችን ተጠቅመው በራሳቸው ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያግዟቸው፡፡

**ምዘና**

- የሀላፊ ጊዜን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤
- የአሁን ጊዜ ግስ የያዙ ዓረፍተ ነገሮችን መለየት መቻላቸውን መገምገም፤
- የአሁን ጊዜ ግሶችን ተጠቅመው ዓረፍ ተነገር መመስረት መቻላቸውን መፈተሽ፡፡
- ባለሶስት አንቀፅ አከራካሪ ድርሰት መፃፋቸውን  መዳሰስ፤

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብባችሁ የአሁን ጊዜ የሚያመላክት ግስ የያዙ አረፍተ ነገሮችን ፊደል ክበቡ፡፡**

ሀ፣ ሐ እና መ ላይ የሰፈሩት አረፍተ ነገሮች በአሁን ጊዜ ግስ የቀረቡ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# ሰብዓዊ እሴቶች

**(ክፍለ ጊዜ 12)**

**የምዕራፉ አላማዎች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- አዳምጠው መልዕክቱን ይመዝናሉ፤
- ሰዎችን ስለማክበር ምንነት ያብራራሉ፤
- ከሌሎች ጋር ምልልስ ያደርጋሉ፤
- የሰብዓዊ እሴቶች አላባውያንን ይዘረዝራሉ፤
- የቀረበላቸውን ጽሑፍ በመመዘን የተገነዘቡትን በአራት አንቀጽ ይጽፋሉ፤

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ✓ እያዳመጡ መመዘን
- ✓ ተመዛኝ ጽሑፍ
- ✓ ኢ-መደበኛ ንግግር
- ✓ ጥምር ቃላት
- ✓ አንብቦ መልዕክቱን መረዳት
- ✓ ነጠላና ብዙ ቁጥር

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ማዳመጥ**
**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

«ዶክተር ካትሪን ሀምሊን" የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎችዎ ከማንበብዎ በፊት፡-

- በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- ምንባቡን በዝግታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በመቀጠልም ምንባቡን ገታ አድርገው የጊዜ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- በትኩረት እንዲከታተሉዎት ምክር ይለግሷቸው፡፡
- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸውም ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡
- የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርሶ መሪነት በቃላቸው እንዲሰሩ ያድረጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡

❖ ለሚሰጡት መልስ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡

ምዘና

- ካዳመጡት ምንባብ ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- ሁሉም ተማሪዎች የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን መስራት መቻላቸውን መቃኘት፤
- ለሚሰጡት ምላሽ ምክንያታዊ መሆናቸውን መዳሰስ፤

## ዶክተር ካትሪን ሀምሊን

ዶክተር ካትሪን ሀምሊን እ.አ.አ በ1924 ሲድኒ አውስትራሊያ ውስጥ ተወለዱ፡፡ እ.አ.አ በ1959 ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ እቅዳቸው ሦስት ሳምንት የመቆየት ብቻ ቢሆንም በርካታ ሴቶች ህክምና እንደሚያስፈልጋቸው በመገንዘብ ከመሄድ ይልቅ መቆየትን መረጡ፡፡ እ.አ.አ በ1974 አዲስ አበባ ውስጥ የመጀመሪያ የሆነውን የፌስቱላ ሆስፒታል አሰሩ፡፡ ይህ ሆስፒታል ከ45 ሺ በላይ ለሆኑ ኢትዮጵያውያን ሴቶችን ከህመም ፈውሶ መደበኛ ህይወታቸውን እንዲመሩ አድርጓል፡፡

ዶክተር ካትሪን ሴቶችን የመርዳት ተግባራቸው ሴቶችን በማከም ብቻ የተገደበ አልነበረም፡፡ አዋላጅ ነርሶችን የማሰልጠን ሕልማቸውን ለማሳካት በ2000 ዓ.ም የሐምሊን አዋላጅ ነርሶች ማሰልጠኛ ኮሌጅ እንዲቋቋም በማድረግ በርካታ ባለሙያዎች በየገጠሩ እንዲሰማሩ ማድረግ ችለዋል፡፡ ዶክተር ካትሪን ሃምሊን ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ያለ እድሜ ጋብቻንና የተራዘመ ምጥን ተከትሎ በሚከሰት ሽንትንና ሰገራን መቆጣጠር ያለመቻል ችግር ይሰቃዩ የነበሩ በርካታ ሺህ ኢትዮጵያዊያንን ሲታደጉ ኖረዋል፡፡

ዶክተር ካትሪን የአዲስ አበባውን ጨምሮ በሃገሪቱ ስድስት የሃምሊን ፌስቱላ ሆስፒታሎችን በማቋቋም ሴቶች ከሚገጥማቸው የፌስቱላ በሽታ በነጻ ታክመው

እንዲወጡ ከማድረግ ባሻገር ይደርስባቸው ከነበረ የመገለልና የስነ ልቦና ስብራት መታደግ ላይ ሰርተዋል፡፡ ለ60 አመታት በኢትዮጵያ የፌስቱላ ህሙማንን በማከም ሰርተዋል፡፡

**መምህር!**

ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ እየተከታተሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሾቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

- ❖ ካዳመጣችሁት ምንባብ በመነሳት ዶክተር ካትሪን ሀምሊንን ኢትዮጵያ እንዲቆዩ ያደረጋቸው ነገር ምን ነበር?
- ❖ ዶክተር ካትሪን ሀምሊን ሴቶችን በተመለከተ ያከናወኗቸው ተግባራት ምን ምን ነበሩ?

በበጎ ትዕዛዝ ላይ ተሰማርተው የበርካታ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ችግርን የቀረፉት ዶክተር ካትሪን ሐምሊን በዋጋ ለማይተመነው አበርክቷቸው በርካታ ሽልማቶችንና ክብሮችን ተቀዳጅተዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡- የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሰብአዊነት ሽልማት፣ የኦርደር ኦፍ አውስትራሊያ ሽልማት፣የቀዶ ጥገና ሀኪሞች ኮሌጅ የክብር ወርቅ ሜዳሊያ ሽልማት፣ የአውስትራሊያ ከፍተኛ ብሄራዊ ሽልማት፣ አለም አቀፍ የጤና ምክር ቤት የላቀ አፈፃፀም ሽልማት፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስነ ህዝብ ሽልማት እንዲሁም የኢትዮጵያ የክብር ዜግነትና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ የክብር ዶክትሬት ተበርክቶላቸዋል፡፡ ከነዚህ ሽልማቶች በተጨማሪ ካትሪን ሐምሊን እ.አ.አ የ1999 እና የ2004 የኖቤል ሽልማት እጩ ሆነው ቀርበው ነበር፡፡

እ.አ.አ በ2009 “ተለዋጭ ኖቤል” በመባል የሚታወቀውና አስቸኳይ ምላሽ ለሚሹ አለም አቀፍ ፈተናዎች ተግባራዊና ተምሳሌታዊ የሆኑ መፍትሔዎችን ላፈለቁ አካላት የሚሰጠው የ”ራይት ላይብሊሁድ ሽልማት” ተበርክቶላቸዋል፡፡ “የኢትዮጵያ እናቶች እናት” በመባል የሚታወቁና የረጅም አመት የማህጸን ሀኪም በመሆን ያገለገሉት ዶክተር ካትሪን ሀምሊን በ96 አመታቸው መጋቢት 14 ቀን 2012 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል፡፡ ስርዓተ ቀብራቸውም በጳውሎስ ወጼጥሮስ ቤተክርስቲያን ተፈፅሟል

**ድህረ ማዳመጥ**

| |
|---|
| **መምህር!**<br>በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በጽሑፍ በማሰራት የተማሪዎቹን የአዳምጦ መረዳት ደረጃ ይፈትሹ፡፡ |

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

## የትምህርቱ አቀራረብ

## ትዕዛዝ

**መምህር!**

- ጭውውትን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎቹ እንዲገለብጡ ያድርጉ፡፡
- በመቀጠልም መፅሃፋቸው ላይ የቀረበላቸውን ጭውውት ለመስራት አራት አራት ሆነው እንዲቧደኑ ያድርጉ፡፡
- ቡድኑ ፆታዊ ስብጥር እንዲኖረው ያድርጉ፡፡
- የተለማመዱትን ክፍል ውስጥ በትዕዛዝ እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፡፡
- ትዕዛዝ ሁለት ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ውይይት ተደርጎባቸው የሚቀርቡ ስለሆኑ ተማሪዎቹን ሶስት ሶስት በማድረግ ያቧድ ኗቸው፡፡

**በመቀጠልም፡-**

- በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ይዘዟቸው፡፡
- በየቡድናቸው እየሄዱም የግልፅነት ጥያቄ ካለ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- በመጨረሻም የተወያዩበትን ሀሳብ በተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በመረጃ ሰጪ ንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- በተሰጧቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረጋቸውን መከታተል፤
- ቡድኑ ፆታዊ ስብጥር እንዳለው መፈተሽ፤
- ጭውውቱን በትዕዛዝ መለማመዳቸውን መቃኘት፤
- ጭውውቱን ካቀረቡ በኋላ ግብረመልስ ይስጧቸው፤ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

## የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

መምህር!

- ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት መማሪያ መፅሃፉ ላይ ያሉትን የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች በማቅረብ በውይይት እንዲሳተፉና እንዲነቃቁ ያድርጉ፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- አያይዘውም ተማሪዎቹ ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡
- ከዚያ ምንባቡን ተማሪዎች በአንቀፅ በአንቀፅ እየተከፋፈሉ በየተራ እንዲያነቡት ያድርጉ፡፡
- ንባቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ ምክንያታዊ ሆነው መልሳቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- አንብበው መገንዘብ መቻላቸውን መፈተሽ፤
- ካነበቡት ጽሑፍ ምን እንደተገነዘቡ ድህረ ንባብ ጥያቄዎችን በማሰራት መገምገም፤
- አካል ጉዳተኛና አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ በንቃት ተሳትፎ ማድረጋቸውን መፈተሽ፤

**መልመጃ አንድ፡-**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡**

**፩. ለ**

**፪. መ**

**፫. ሀ**

**፬. መ**

መልመጃ ሁለት

ከዚህ በታች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ አዳዲስ ቃላት ቀርበዋል፡፡ ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አገባብ መሰረት ፍቻቸውን ስጡ፡፡

ሀ. መንደር/ ሰፈር

ለ. ታስተካክላለች/ ታቃናለች

ሐ. ራሰ በራ ወይም ጸጉሩ የተመለጠ

መ. ሳይጠሩ የእተው

ሠ. እንደነገሩ ይዤ

ረ. ጠርዝ

ሰ. ሰዎች ስራን በጋራ ሲሰሩ የሚያወጡት ትብብርን የሚያመለክት

መልመጃ ሶስት

ከዚህ በታች ከምንባቡ የወጡ ቃላት በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡትን ቃላት በመምረጥና ባዶ ቦታው ውስጥ በማስገባት ዓረፍተ ነገሩን አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

| | |
|---|---|
| ፩. ዋልጌ | ፭. ወሸካታ |
| ፪. የቂም ዶሴ | ፮. ልህቀት |
| ፫. ጉፍታ | ፯. ፊት ማሳየት |
| ፬. ቀዬ | ፰. ጥሩር |

ክፍል አራት፡- መጻፍ

የትምህርቱ አቀራረብ

ትዕዛዝ

መምህር!

- በቅድሚያ ተማሪዎች በመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ የቀረበላቸውን የቢጋር ማስታወሻ በደብተራቸው እንዲገለብጡ ይዘዟቸው፡፡
- የቀረበላቸውን ቢጋር መነሻ በማድረግ በተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ቢጋር እንዲያዘጋጁ ያድርጓቸው፡፡
- በመቀጠልም ባዘጋጁት ቢጋር መሰረት ባለ አራት አንቀፅ እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- የፃፉት አንቀፅ ባዘጋጁት ቢጋር መሰረት መሆኑን ይዩላቸው፡፡ ማስተካከያም ያደርጉላቸው፡፡
- በተጨማሪም በሚፈልጉት ርዕሰ ጉዳይ ላይ አመዛዛኝ ፅሁፍ እንዲፅፉ ትዕዛዝ ይስጧቸው፡፡
- በመጨረሻም ግብረ መልስ ይስጧቸው፤ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ንድፍ (ቢጋር)ን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መፃፋቸውን መፈተሽ፤
- ቢጋር አዘጋጅተው በተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ባለ አራት አንቀፅ አመዛዛኝ ድርሰት መፃፋቸውን ማረጋገጥ፤
- በፈለጉት ርዕሰ ጉዳይ ላይ አመዛዛኝ ፅሁፍ መፃፋቸውን መገምገም፤

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

መምህር!

- ✓ በመጀመሪያ ለተማሪዎች የድርብ ቃላትን ምንነት ያስረዷቸው፤
- ✓ አጭር ማስታዎሻም ያስይዟቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- ✓ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ጥምር ቃላትን በማስገባት እንዲጠቀሙ ያድርጓቸው፡፡

**ምዘና**

- የጥምር ቃላትን ምንነት በተመለከተ ማስታወሻ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤
- በዓረፍተ ነገር ውስጥ ጥምር ቃላት መጠቀም መቻላቸውን መገምገም፤

### መልመጃ አንድ

**በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉ ጥምር ቃላትን ተጠቅማችሁ ከታች ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

፩. ሰላማዊ ሰልፍ

፪. መቅረፀ-ድምፅ

፫. ሽክላ ድስት

፬. ብረት-ምጣድ

፭. ቤተ-መንግስት

፮. አውራ ጎዳና

፯. አየር-መንገድ

**መልመጃ ሁለት**

**በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉ ውስብስብ ቃላትን ተጠቅማችሁ ከታች ያሉትን አረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ።**

፩. ምጣኔ ሃብታዊ

፪. እየጨፈጨፉ

፫. መልዕክቶችን

፬. ይፈጥርላቸዋል

፭. ኑሯቸውን

፮. አገልግሎታቸውን

፯. ለተማሪዎቻቸው

፰. ከተከታተልናቸው

## ክፍል ስድስት፦ ሰዋስው

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

መምህር!

- ✓ ነጠላ እና ብዙ ቁጥርን በተመለከተ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጓቸው፤
- ✓ በምሳሌ አስደግፈው መጠነኛ ገለፃም ያድርጉላቸው፡፡

በመቀጠልም፦

- ✓ ነጠላ እና ብዙ ቁጥር ቃላትን በዓረፍተ ነገር ውስጥ እንዲጠቀሙ ያድርጓቸው፡፡

ምዘና

- ነጠላ እና ብዙ ቁጥርን በተመለከተ አጭር ማስታዎሻ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤
- ነጠላ እና ብዙ ቁጥርን በትክክል መጠቀማቸውን መገምገም፤

**መልመጃ አንድ፡**

**የሚከተሉትን ስሞች "-ኣት" የሚለውን ምዕላድ በመጨመር ወደ ብዙ ቁጥር ለውጡ፡፡**

፩. ዓመታት

፪. ዲያቆናት

፫. ወራት

፬. ካህናት

፭. ቃላት

# ምዕራፍ አራት

# አጭር ልቦለድ

**(12 ክፍለ ጊዜ)**

**የምዕራፉ አላማዎች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- አዳምጠው ተመሳሳይ ታሪክ ይናገራሉ፤
- ስለ አጭር ልቦለድ ምንነት ይገልጻሉ፤
- በጽሑፍ ውስጥ መሸጋገሪያ ቃላትን ይጠቀማሉ፤
- የአጭር ልቦለድ አላባውያንን ይዘረዝራሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ታሪክ መንገር
- መመሪያን መገንዘብ
- ፈሊጣዊ አነጋገሮች
- መሸጋገሪያ ቃላት
- የማይዘወተሩ (ኢ-ተዘውታሪ) ቃላት
- ሐረግ

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የሕይወት ቅዳጆች

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ቅድመ ማዳመጥ

### ትዕዛዝ

**መምህር!**

« **የህይወት ቅዳጆች**" የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎችዎ ከማንበብዎ በፊት፡-

- በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

### ጊዜ ማዳመጥ

### ትዕዛዝ

- ምንባቡን በዝግታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በመቀጠልም ምንባቡን ገታ አድርገው የጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡

- በትኩረት እንዲከታተሉዎት ምክር ይለግሷቸው፡፡
- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸውም ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ሲሰሩ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡
- የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርሶ መሪነት በቃላቸው እንዲሰሩ ያድረጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡
- ለሚሰጡት መልስ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- ካዳመጡት ምንባብ ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- ሁሉም ተማሪዎች የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መስራት መቻላቸውን መቃኘት፤
- ለሚሰጡት ምላሽ ምክንያታዊ መሆናቸውን መዳሰስ፤

## የሕይወት ቅዳጆች

….ሰለሞን ያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ፊት ለፊት ያሉ መደዳ የንግድ ቤቶች በጀርባቸው ካዘልዋቸው መኖርያ ቤቶች አንዱን ባለ አንድ ክፍል በአንድ መቶ ሃያ ብር ተከራይቶ ይኖራል፡፡ የተንጋደደውን የግቢውን የቆርቆሮ አጥር በር ከፍቶ እንደገባ በቀጭን ቦይ የሚወርደውን የሽንት ቤቱን እንባ ተራምዶ ዘለቀ፡፡ እዚህ ግቢ ተከራይቶ ከገባ ጀምሮ የመንደርተኛው መጸዳጃ የአስመጥጡኝ ለቅሶውን እንዳሰማ አለ፡፡ እንባው አንዴ እየጠቆረና እየወፈረ፣ አንዴ እየቀጠነና ውሃ እየመሰለ

ክረምት ከበጋ ግቢውን አቋርጦ ቢፈስም፣ የመጸዳጃ ቤቱን ለቅሶ እዚህ ግባ ያለው የለም፡፡

ሰለሞን የቤቱን በር ከፍቶ እንደገባ ባለረዥርም ማንጠልጠያ የመጻህፍት መያዣ ቦርሳውን ፍራሹ ላይ ወረወረው፡፡ ሁለቴ ተራመደና በወር ሰላሳ ብር በሚከፍልበት የሽቦ አልጋ ላይ በጀርባው ተንጋለለ፤ ደክሞታል፡፡ ረሃቡ ነው ወይስ ሀሳብ ያደክማል! አልጋው ላይ እንደተንጋለለ፣"ግን በእግር መጓዝ ነው በሃሳብ መጓዝ የበለጠ የሚያደክመው?" እራሱን ጠየቀ፡፡ በረሃቡ ላይ ሀሳብ መጨመር አልፈለገም፤ አይኑን ጨፈነ፤ በድርጊቱ ፈገግ አለ፡፡ መጨፈኑ አለማየት እንጂ አለማሰብ እንደማያስችለው ሲገባው "ምናለ ህሊናንም መጨፈን ቢቻል" ብሎ አሰበ፡፡

**መምህር!**

ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ እየተከታተሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሾቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

- ሰለሞን ቤት ውስጥ አሉ ተብለው ከተዘረዘሩ ቁሳቁሶች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ጥቀሱ?
- ከዚህ በኋላ ሰለሞን ምን የሚያጋጥመው ይመስላችኋል?

ወዲያው “ሰሌ” የሚል የሴት ድምጽ ጠራው፡፡

“ጠረጴዛ ላይ አስቀምጪው ድርሳን፡፡” አለ፣ አይኑን እንደጨፈነ፡፡ በምሳ ሰዓት ወደ ግቢ ከመጣ በመጀመሪያ ቤቱ የምትመጣው ድርሳን ናት፡፡ ድርሳን የቤት አከራዩ የእንጀራ ጋጋሪዋ የእትዬ ውዴ ልጅ ናት፡፡ ሁለት እንጀራ በማይካ ዝርግ ሳህን በላዩ ላይ ቢጫ ዳንቴል ጣል አርጋ ከች ትላለች፡፡ ሂሳቡን አስቦ በወር ይከፍላቸዋል፡፡

“ሰሌ ምነው? አመመህ እንዴ? እንጀራውን እያስቀመጠች ጠየቀችው፡፡”

“አላመመኝም፡፡ እርቦኝ ነው!”አሁንም አይኑን እንደጨፈነ መለሰ፡፡

“ቀልደህ ሞተሃል!” ብላው ወጣች፡፡ ሰለሞን ለጓደኞቹ የደበቀውን ረሃቡን ተናግሮ ንዴቱን ተወጣ፡፡

“ግን ያላመነችኝ ለምንድን ነው? እራሱን ጠየቀ፡፡ “እንዴት ታምናለች፡”የሁለተኛ ድግሪ ተማሪ መሆኔን እንጂ ሌላውን ችግሬን መች አውቃ አሁንም አይኑን አልገለጠም፡፡ የቤቱ ብርሃን ሲደበዝዝ፣ቆሌውን ሲከብደው “ወይኗ” ብሎ ተጣራ፡፡

"አቤት ጋሼ ሰለሞን" አለችውና በትናንሽ እግሮችዋ ወደ ውስጥ ዘለቀች፡፡

"ፍራሹ ጫፍ ላይ ሁለት ብር አለልሽ፡፡"

"የአንድ ብር ስኳር፣ የሃምሳ ሳንቲም ሻይ ቅጠል"

"ጋሽ ሰለሞን ብሩ የለም!›

"ቦርሳውን ዞር አድርጊና በደንብ ፈልጊው፡፡"

"አግኝቼዋለሁ፡፡ መልሱን ጋሽ ሰለሞን?"

" ውሰጂው፡፡" እየሮጠች ወጣች፡፡

ስትመለስ ሰለሞን ተነስቷል፡፡ አይኑን አፍጥጦ እንጀራ በሚጥሚጣ ይበላል፡፡ ከማይበላው አንድ እንጀራ ላይ ቆርሶ በሚጥሚጣው ላይ አንደባሎ ጠቀለለና ሰጣት፤ ሚጥሚጣ ትወዳለች፡፡ ገና አስር አመቷ ቢሆንም የሚያቃጥል ነገር ነፍሷ ነው፤ የሚለበልባትን ህይወት ለሰስ ያደርግላታል…፡፡

***(በድሉ ዋቅጂራ 2006፣19-22፣ያልተከፈለ ስለት መጠነኛ መሻሻል ተደርጎበት)***

**ድህረ ማዳመጥ**

**መምህር!**

በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በጽሑፍ በማሰራት የተማሪዎቹን የአዳምጦ መረዳት ደረጃ ይፈትሹ፡፡

**መልመጃ አንድ**

**ያዳመጣችሁትን ጽሑፍ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

፩. ሐ

፪. ሐ

፫. መ

፬. መ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- የንግግርን መመሪያ በተመለከተ አጭር ማስታወሻ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎቹ እንዲገለብጡ ያድርጉ፡፡
- በመቀጠልም ተማሪዎች የአጭር ልቦለድ አላባውያንን በተመለከተ አንዱ ተማሪ ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ ደስ ያለውን የቡድን አባል እንዲናገር እድል በመስጠት ተራ በተራ እየተቀባበሉ ያላቸውን ሃሳብ በቃል እንዲገልፁ ያድርጓቸው፤
- ሁሉም የቡድኑ አባላት ተሳታፊ መሆን እንደሚኖርባቸው መመሪያ ይስጧቸው፡፡
- በመጨረሻም ከየቡድኑ አንድ አንድ ተወካይ ተማሪ በመነሳት ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- የንግግርን መመሪያ በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- መመሪያ በመሰጣጣት ሀሳባቸውን መግለፅ መቻላቸውን መገምገም፤

- ሁሉም ተማሪዎች መሳተፋቸውን መዳሰስ፤
- በተወካያቸው አማካኝነት ያቀረቡትን ሀሳብ መገምገም

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

### የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት መማሪያ መፅሃፉ ላይ ያሉትን የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች በማቅረብ በውይይት እንዲሳተፉና እንዲነቃቁ ያድርጉ፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- ተማሪዎቹ ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡
- ንብቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ ምክንያታዊ ሆነው መልሳቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤

❖ በመጨረሻም እርማትም ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

❖ አንብበው መገንዘብ መቻላቸውን መፈተሽ፤

❖ ካነበቡት ጽሑፍ ምን እንደተገነዘቡ ድህረ ጥያቄዎችን በማሰራት መገምገም፤

❖ አካል ጉዳተኛና አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ በንቃት ተሳትፎ ማድረጋቸውን መፈተሽ፤

**መልመጃ ሁለት**

**በምንባቡ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

፩. እውነት

፪. እውነት

፫. ሀሰት

፬. ሀሰት

፭. እውነት

**መልመጃ ሶስት፡-**

**ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ መልሱ፡፡**

፩. መ

፪. ሐ

፫. መ

፬. ሐ

፭. ሀ

**ፈሊጣዊ ንግግር**

ፈሊጥ፡- እያንዳንዱ ቃል በተናጠል ከሚሰጠው ትርጉም በተጨማሪ የተለየ ፍች የሚያስገኝበት የቃላት ቅንጅት ነው፡፡

- ❖ አንድ ሀሳብ ከመደበኛው /ከቀጥታ/ አገላለፅ በተለየ መልኩ ክብደትና ውበትን ተጎናፅፎ ለአድማጭ እንዲደርስ የሚያደርግ የአነጋገር ስልት ነው፡፡
- ❖ ፈሊጦች የተናጋሪውን ቋንቋ ውበትና ለዛ በማላበስ የአድማጭን ስሜት የሚኮረኩሩ ቅመሞች ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-

-ቀለም ያዘ-----ተረዳ፣ አወቀ

-አደብ ገዛ----ጭምት ሆነ

-ፊት ነሳኝ---አገለለኝ፣ አራቀኝ

-ሰማይ ቅርቡ----ወሬኛ፣ የትዕዛዝ ሰው ያልሆነ

-ቀኝ እጅ----መከታ፣ አለኝታ

**መልመጃ አራት**

ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡

፩. ለ

፪. መ

፫. ሀ

፬. ሐ

፭. ለ

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

**መምህር!**

- በቅድሚያ ተማሪዎቹ መሸጋገሪያ ቃላትን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ እንዲይዙ ያድርጓቸው፤
- በመቀጠልም የቀረቡላቸውን የመሸጋገሪያ ቃላት በመጠቀም የዓረፍተ ነገሮችን ክፍት ቦታ በማሟላት እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- በተጨማሪም «ታሪኬ» በሚል ርዕስ ባለአራት አንቀፅ ተራኪ ድርሰት ፅፈው ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፤
- በመጨረሻም ግብረመልስም ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- መሸጋገሪያ ቃላትን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መፃፋቸውን መፈተሽ፤
- የቀረቡላቸውን መሸጋገሪያ ቃላት በዓረፍተ ነገሮቹ ክፍት ቦታ ላይ ማስገባት መቻላቸውን መዳሰስ፤
- «ተሪኬ» በሚል ርዕስ ባለ አራት አንቀፅ ተራኪ ድርሰት መፃፋቸውን ማረጋገጥ፤

**መልመጃ አንድ፡-**

**በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ከዚህ በታች ከቀረቡት መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሀረጋት መካከል በመምረጥ አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

፩. ከዚህ በማያያዝ

፪. ወደፊት

፫. በመቀጠል

፬. እስከዚህ ድረስ

፭. ከዚህ ቀጥሎ

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ✓በመጀመሪያ ለተማሪዎች ያልተለመዱ (ኢ-ተዘውታሪ) ቃላትን ምንነት ያስረዷቸው፡፡
- ✓በመቀጠልም አጭር ማስታወሻ ያስይዟቸው፡፡
- ✓በተጨማሪም ምሳሌዎችን በመጠቀም ያልተለመዱ ቃላት የሚባሉትን እንዲለዩ ያሳይዋቸው፡፡
- ✓ከዚያ ያልተለመዱ ቃላትን ከፍችዎቻቸው ጋር ማዛመድ እንዲችሉ

ያግዟቸው፡፡

**ምዘና**

- ያልተለመዱ ቃላትን ምንነት በተመለከተ ማስታወሻ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤
- አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሸ፤
- የቀረቡላቸውን ያልተለመዱ ቃላት ከፍቻቸው ጋር ማዛመድ መቻላቸውን መገምገም፤

**መልመጃ አንድ**

**በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ኢ-ተዘውታሪ ቃላት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ፍችዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

፩. መ

፪. ሸ

፫. ሰ

፬. ረ

፭. ሐ

፮. ለ

፯. ሠ

**የልቦለድ ዘዴዎች**

አንድ ድርሰት ተገቢውን ቅርጽና ይዘት አግኝቶ አንድ ውቅር እሚሆነው አላባውያኑ በተገቢው መጠንና ቅደም ተከተል ተዋህደውና ተሳስረው ሲኖሩ ነው፡፡ ይህን መተሳሰር ከሚያስገኙት መሃል ደግሞ ምልልስ፣ ገለፃ፣ ምልሰትና ንግር ዋናዎቹ የአተራረክ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ቀጥሎ እነዚህን ዘዴዎች ባጭር ባጭሩ እንመለከታለን፡፡

**ምልልስ፡-** በእውኑ አለም በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ የሀሳብ ወይም የንግግር መለዋወጥ አለ፡፡ ሁለት ሰዎች ባላቸው ግንኙነት መሰረት በየአጋጣሚው

በሆነ ጉዳይ ላይ ሲነጋገሩና ሀሳብ ለሀሳብ ሲለዋወጡ እንሰማለን፡፡ እንዲህ ያለው የሀሳብ መለዋወጥ ምልልስ በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ ምልልስ በዘዴነቱ የገጸ ባህሪያቱን ስሜት ፣ አላማ ችግር እንዲሁም ስነልቦናዊ መልክ ማሳያ ነው፡፡

**ገለጻ፡-** ገለጻ የተቀረጹትን ገጸባህሪያት መልክ ቁመና አለባበስና ስሜት የሚንቀሳቀሱበትንና የሚኖሩበትን አካባቢ እንዲሁም የአየር ሁኔታና ድባብ በማቅረብ ታሪኩ እውነት እንዲኖረው ከማድረጉም በላይ አንባቢው ገጸባህሪያቱን ከነአካባቢያቸው እንዲመለከታቸው ያስችላል፡፡

**ንግር፡-** ንግር በታሪኩ ሂደት ወደፊት ለሚፈጸም ድርጊት አጋጣሚ ወይም ሁኔታ የሚሰጥ ፍንጭ ወይም ጥቆማ ነው፡፡ "ንግር በስነ-ጽሁፍ ስራ ውስጥ አስቀድሞ ማሳየት ማመልከት ወይም መጠቆም " ነው፡፡ በንግር ስለ ትልሙ አካሄድ ስለግጭቱ ሁኔታ እንዲሁም ስለገጸባህሪያቱ ማንነት በታሪኩ ውስጥ ስለሚገጥማቸው አቢይ ነገር አስቀድሞ ለአንባቢ እውቂያ ይሰጣል፡፡

**ምልሰት፡-** ምልሰት አሁን በመተረክ ካለው ዋነኛ የታሪኩ ክፍል ወይም በትልሙ ጉዞ ከአንድ ዋነኛ ድርጊት ወይም ሁነት አስቀድሞ የተፈጸመው ድርጊት ወይም ሁነት በማስገባት የሚቀርብ የአተራረክ ዘዴ ነው፡፡ በገጸ ባህሪው ህይወት ወደኋላ በመሄድ የነበረውን ሁኔታ ወይም ይበልጥ ያሳውቃል፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

**መምህር!**

- ✓ ሐረግን በተመለከተ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በምሳሌ አስደግፈው መጠነኛ ገለፃም ያድርጉላቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- ✓ ሐረጋትን ተጠቅመው ዓረፍተነገር እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ግበረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- ሐረግን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤
- ሐረጋትን ተጠቅመው ዓረፍተነገር መመስረታቸውን መገምገም፤
- በዓረፍተነገር ውስጥ የተሰጧቸውን ሀረጋት መለየት መቻላቸውን መፈተሽ፤

**መልመጃ አንድ**

**በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ሐረጎች አይነት በምሳሌው መሰረት ጥቀሱ፡፡**

፩. መስተዋድዳዊ ሀረግ

፪. ቅፅላዊ ሀረግ

፫. ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ

፬. ስማዊ ሀረግ

፭. ግሳዊ ሀረግ

# ምዕራፍ አምስት
# ሥነ ህዝብ

(ክፍለ ጊዜ 9)

**ከዚህ ትምህርት የሚጠበቅ ውጤት፣ ይህንን ምዕራፍ ተምረው ከጨረሱ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- በአትኩሮት አዳምጠው ጽሑፉን ይገልጻሉ፤
- ስለ ሕዝብ ብዛት ምንነት ያብራራሉ፤
- የሕዝብ ብዛት በኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ይተነትናሉ፤
- ተራኪ ጽሑፍ ጽፈው ይመዝናሉ፤

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ማዳመጥን መመዘን
- ውስብስብ መረጃዎች
- ምክንያትና ውጤት
- ተራኪ ጽሑፍ
- እማሪያዊ ፍች
- ገቢርና ተገብሮ

# ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## የህዝብ ቁጥር መጨመር እንደ መልካም አጋጣሚ

## የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

«የሕዝብ ቁጥር መጨመር እንደ መልካም አጋጣሚ" የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎችዎ ከማንበብዎ በፊት፡-

- በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- ምንባቡን በዝግታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በመቀጠልም ምንባቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- በትኩረት እንዲከታተሉዎት ምክር ይለግሷቸው፡፡
- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸውም ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ሲሰሩ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠልም ምንባቡን እየደጋገሙ በማንበብ የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርሶ መሪነት በቃላቸው እንዲሰሩ ያድረጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡
- ለሚሰጡት መልስ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- ካዳመጡት ምንባብ ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- ሁሉም ተማሪዎች የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን መስራት መቻላቸውን መቃኘት፤
- ለሚሰጡት ምላሽ ምክንያታዊ መሆናቸውን መዳሰስ፤

## የህዝብ ቁጥር መጨመር እንደ መልካም አጋጣሚ

የውጭ አገር ኩባንያዎች፤ የተለያዩ አገራት ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ላይ ፍላጎት እያሳዩ የመጡት ኢትዮጵያ ከሌሎች የአፍሪካ አገራት የተሻለ የኢንቨስትመንት አካባቢ ስላላት ብቻ አይደለም። ያላት መሰረተ ልማትም ያን ያህል ሳቢ ሆኖ አይደለም። ህዝብን በአግባቡ አሠልጥኖና አበልጽጎ ጠንካራ የሥራ ባህልን ማስረፅ ከተቻለ የህዝብ ብዛት በራሱ ሀብት ስለሆነ ነው። ህዝብ ከሌለ ሀብት የለም። በአንድ አገር ላይ ጠንካራ የስራ ባህል ያለው ህዝብ ቁጥር ሲጨምር የሀገሪቷም ሀብት እየጨመረ እና እያደገ እንደሚሄድ እሙን ነው።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር 70 በመቶ ወጣት እና ሰርቶ ያልደከመ ነው። ይህንን ትኩስ ጉልበት ደግሞ ወደስራ ማሰማራትና አልሚ እንዲሆን ማድረግ መንግስትን ጨምሮ የእያንዳንዱ ዜጋ ሀላፊነት ነው። አንዳንድ ቦታ ላይ የኑሮ ውድነት መባባስ፣ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን፤ በከተሞች አካባቢ የመሬት መወደድ ሁሉ ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ይያያዛል። ነገር ግን ህዝብን ማሰልጠን፤ ማስተማር፤ ህግና ሥርዓትን እንዲያከብር ማድረግ፤ ምቹ ፖሊሲ አውጥቶ መደላድል በመፍጠር እያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት እንዲሰማው ማድረግ ከተቻለ የህዝብ ቁጥር መጨመር እንደበረከት እንጂ እንደመርገምት ሊታይ አይችልም።

በምቹ ሁኔታ ያደጉ ልጆች ተመልሰው አምራች ኃይል የመሆናቸው ጉዳይ አጠያያቂ አይደለምና በአንዳንድ የአደጉ አገሮች ሴቶች ሲወልዱ ለተወለዱት ሕፃናት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ሲባል ከፍተኛ ዕርዳታ ይሰጣቸዋል። አምራች ዜጋ ሲበራከት ደግሞ አገር ያድጋል። የሚወለዱት ህፃናት በደንብ ከተያዙ፤ ሁኔታዎች ሁሉ የተስተካከሉ ከሆኑ፤ ሳይንስና ቴክኖሎጂው ከተስፋፋ የህዝብ ብዛት ስጋት ከመሆን ይልቅ ተስፋ ይሆናል።

**መምህር!**

ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ እየተከታተሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሾቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

- እስካሁን ካዳመጣችሁት በመነሳት የበለፀገች አገር ማግኘት የሚቻለው መቼ ነው?

- ባልተመቻቸ ሁኔታ የሚወለዱ ልጆች በሀገር ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ይመስላችኋል?

ከዚህ በተቃራኒው ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ የተወለዱ ልጆች የሚያድጉበት ሁኔታ ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ ቤተሰብ የማሳደግ አቅሙ በማነሱ የልጆቹን የምግብ ፍላጎት ካለማሟላቱ በተጨማሪ ጥሩ የትምህርት እድል የማያገኙ ከሆነ፣ ልጆቹ አድገው ለአገር ይተርፋሉ ብሎ ከማሰብ ይልቅ የአገር ሸክም ይሆናሉ የሚል ስጋት ውስጥ መግባቱ ሀቅ ነው፡፡ ልጆች በደንብ ተኮትኩተው የሚያድጉ ካልሆነ ፈጣሪዎች ሆነው ከራሳቸው አልፈው ለአገር ከመትረፍ ይልቅ የአገር ሸክም የሚሆኑበት ዕድል ያመዝናል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ የሚያመርተው የሰው ሀይል ጥቂት ሲሆን የማምረቻ መሳሪያውም ውስን ነው፡፡ የሚመረተው ሀብትም ውስን በመሆኑና ብዙዎች ስለሚሻሙት በጥቂት የህብረተሰብ ክፍሎች የሚመረተው በሸሚያ አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ ይህ ደግሞ ኑሮን ስለሚያስወድድ ድህነት ይባባሳል፡፡ የህዝብ ቁጥር መጨመር በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ብዙ ጉዳት አለው፡፡ በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ በተለይ በኢንዱስትሪ እና በማዕድን ላይ ሳይሰማሩ 80 በመቶ በግብርና ላይ የሚተዳደር

ህዝብ ባለበት አገር ውስጥ የሰው ቁጥር መጨመር ጉዳት አለው፡፡ በትምህርት አሰጣጥ፤ በጤና አጠባበቅና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ጫና ይፈጥራል፡፡

የህዝብ ቁጥር መጨመርና የሀብት በቂ አለመሆን የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በዕድገት ላይ ነች፡፡ በየቦታው የኢንዱስትሪ ፓርኮች እየተሠሩ ነው፡፡ ይህ ቢቀጥልና ወጣቱ ሥራ ላይ ቢሰማራ፤ መረጋጋት ቢኖር የህዝብ ብዛት ችግሩ አሳሳቢ አይሆንም፡፡ የህዝብ ቁጥር እንዳይጨምር ከመሥራት ይልቅ የሰው ኃይሉን ከኢኮኖሚው ጋር ማጣጣም፤ የሚወለደውም ራሱን የሚችልና ለአገር የሚተርፍ እንዲሆን መሥራት ላይ ትኩረት መደረግ አለበት፡፡

በመሬትም ሆነ ከመሬት ሥር የተፈጥሮ ሀብት አለ፡፡ ይህን ሀብት ለመጠቀም ደግሞ ባለሀብቶች በጎ ተፅዕኖ ማሳደር አለባቸው፡፡ ከመንደር እድር ጀምሮ የሲቪክ ማህበራት ሚናቸውን ከተወጡ የህዝብ ቁጥር ቢጨምርም ተስፋ እንጂ ስጋት አይሆንም፡፡ ባንኮች፣ መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ኃላፊነታቸውን ከተወጡ፤ ልጆችን በማስተማር አገርን የመታደግ እንቅስቃሴ ከተካሄደ የህዝብ ቁጥር መጨመር ፈተና ሳይሆን ሲሳይ ይሆናል፡፡

(ምህረት ሞገስ፣ አዲስ ዘመን፣ ጥር 25/2012 ዓ.ም፤ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ድህረ ማዳመጥ

**መምህር!**

በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች በጽሑፍ እንዲሰሩ በማድረግ የተማሪዎቹን የአዳምጦ መረዳት ደረጃ ይፈትሹ፡፡

**መልመጃ ሁለት**

**ለሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

፩. መነመነ

፪. ደለደለ

፫. በረከት

፬. ኮተኮተ

፭. ትኩረት

# ክፍል ሁለት፡- መናገር

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ❖ ተማሪዎች የምክንያትና ውጤት ትስስርን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ እንዲይዙ ያድርጉ፡፡
- ❖ በመቀጠልም ከዓረፍተ ነገር ውስጥ ምክንያትና ውጤቱን ለይተው እንዲገልፁ ያድርጓቸው፤
- ❖ ሁሉም ተማሪዎች መስራት እንደሚኖርባቸው መመሪያ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፤ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ❖ ምክንያትና ውጤትን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- ❖ ከዓረፍተነገር ውስጥ ምክንያትና ውጤቱን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- ❖ ሁሉም ተማሪዎች ምክንያትና ውጤትን መለየት መቻላቸውን መገምገም፤

# ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

**ቅድመ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

*መምህር!*

- ❖ ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት መማሪያ መጽሐፉ ላይ ያሉትን የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች በማቅረብ በውይይት እንዲሳተፉና እንዲነቃቁ ያድርጉ፡፡
- ❖ በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- ❖ በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- ❖ ተማሪዎች ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ንባቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- ❖ ከምንባቡ ውስጥ የምክንያትና ውጤት ትስስር የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮችን በማውጣት ምክንያትና ውጤታቸውን እንዲለዩ ያግዟቸው፤
- ❖ የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ሲሰሩ በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ ምክንያታዊ ሆነው መልሳቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤

❖ በመጨረሻም እርማትም ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

❖ አንብበው መገንዘብ መቻላቸውን መፈተሽ፤

❖ ካነበቡት ጽሑፍ ምን እንደተገነዘቡ ድህረ ንባብ ጥያቄዎችን በማሰራት መገምገም፤

❖ የምክንያትና ውጤትን ትስስር ማሳየት የሚችሉ ዓረፍተ ነገሮችን መለየት መቻላቸውን መዳሰስ፤

❖ ከዓረፍ ተነገሩ ውስጥ ምክንያቱንና ውጤትን ለይተው ማሳየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

**፩. ሀሰት**

**፪. እውነት**

**፫. ሀሰት**

**፬. እውነት**

**፭. እውነት**

**መልመጃ ሁለት**

**ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ መልሱ።**

**፩. ሀ**

**፪. ሐ**

**፫. ለ**

**፬. መ**

**፭. ሐ**

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

መምህር!

- በቅድሚያ ተማሪዎችን ተራኪ ድርሰትን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ ያስይዟቸው።
- በመቀጠልም የአንድን ታዋቂ ሰው  የሕይወት ታሪክ በአምስት አንቀፅ እንዲጽፉ ያድርጓቸው።
- በመጨረሻም ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፤

- በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- ተራኪ ድርሰትን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መፃፋቸውን መፈተሽ፤
- የታዋቂ ሰውን የሕይወት ታሪክ በአምስት አንቀፅ መፃፋቸውን ማረጋገጥ፤

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ✓ በመጀመሪያ ለተማሪዎች የቃላትን እማሪያዊ ፍች እና ፍካሬያዊ ፍች ምንነት ያስረዷቸው፤
- ✓ በመቀጠልም አጭር ማስታወሻ ያስይዟቸው፡፡
- ✓ በተጨማሪም ምሳሌዎችን በመጠቀም የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

**ምዘና**

- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ምንነት በተመለከተ ማስታወሻ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤
- ለቀረቡላቸው ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መስጠት መቻላቸውን መገምገም፤

**መልመጃ አንድ**

የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች በሰንጠረዡ በቀረበው ምሳሌመሰረት አስቀምጡ፡፡

| ቃል | እማሬያዊ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|
| ንብ | ማር አምራች በራሪ ፍጡር | ታታሪ፣ ትጉህ፣ ሰራተኛ |
| ዱባ | እንደድንች ተከትፎ ወጥ ተሰርቶ የሚበላ | ክብ፣ ድብልብል |
| ቋንጣ | ተዘልዝሎ የደረቀ ስጋ | ቀጭን |
| አንበሳ | የሚያስፈራ የዱር አውሬ | ጀግና |
| ተልባ | የቅባት እህል | በአቋሙ የማይፀና፣ ጊዜ አይቶ የሚከዳ |
| እንጀራ | ከጤፍና ከመሳሰሉት ነገሮች የሚሰራ የምግብ አይነት | ስራ፣ መተዳደሪያ |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

መምህር!

- ✓ ገቢርና ተገብሮ ግሶችን በተመለከተ በመማሪያ መፅሀፉ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በተጨማሪም በምሳሌ አስደግፈው መጠነኛ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- ✓ ገቢርና ተገብሮ ግሶችን ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

ምዘና

- ገቢርና ተገብሮ ግሶችን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤
- ገቢርና ተገብሮ ግሶችን ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር መመስረት መቻላቸውን መገምገም፤

# ምዕራፍ ስድስት

# በረሃማነት

**(ክፍለ ጊዜ 9)**

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ከጨረሱ በኋላ፡-

- አዳምጠው እየተነተኑ ጽሑፉን ይመዝናሉ፤
- በተሰጣቸው ርእስ ላይ ውይይት ያደርጋሉ፤
- የበረሃማነትን ምንነት ይገልፃሉ፤
- በረሃማነት የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ያብራራሉ፤
- የተሰጣችሁን ጽሑፍ በማንበብ ማጠቃለያ ይሰጣሉ፤
- የገላጭ ጽሑፍ መዋቅርን ይመዝናሉ፤
- ሀሳባቸውን ለመግለጽ ፍካሬያዊ ፍች ይጠቀማሉ፤
- የዓረፍተ ነገሮችን አገልግሎት ይፅፋሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ✓ ያዳመጡትን መተንተንና መመዘን
- ✓ ውይይት ማድረግ
- ✓ ገላጭ ጽሑፍ
- ✓ ፍካሬያዊ ፍች
- ✓ የዓረፍተ ነገር አገልግሎት

 **ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ**

**የምድራችን ጀግና**

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ቅድመ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

መምህር!

«**የምድራችን ጀግና**" የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎችዎ ከማንበብዎ በፊት፡-

- በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- ምንባቡን በዝግታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በመቀጠልም ምንባቡን ገታ አድርገው የጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- በትኩረት እንዲከታተሉዎት ምክር ይለግሷቸው፡፡
- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸውም ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ሲሰሩ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠልም ምንባቡን እየደጋገሙ በማንበብ የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርሶ መሪነት በቃላቸው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡
- ለሚሰጡት መልስ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- ካዳመጡት ምንባብ ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- ሁሉም ተማሪዎች የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መስራት መቻላቸውን መቃኘት፤
- ለሚሰጡት ምላሽ ምክንያታዊ መሆናቸውን መዳሰስ፤

## የምድራችን ጀግና

ዶክተር ተወልደ ብርሃን ገብረ እግዚአብሔር የዕፀዋት ዘረመል እንዲቀጥል፣ የተስተካከለ ሥነ ኑረትና ሚዛናዊ የአየር ንብረት እንዲኖር፣ የምድሪቱ የተፈጥሮ ጸጋ በድርቅና በፀሐይ ሙቀት ምክንያት እንዳይገፈፍ፣ ዕፀዋት በጎርፍ ምክንያት ከለም አፈር ጋር ተጠራርገው እንዳይሄዱና ምድራችን ምድረ በዳ እንዳትሆን ከልጅነታቸው ጊዜ አንሥቶ በዕፀዋት ላይ ልዩ ትኩረት አድርገው ሲመራመሩ የኖሩና ለውጤትም የበቁ ሳይንቲስት ናቸው። የዕፀዋት ስያሜ ፕሮጀክት ተግባራዊ እንዲሆን ካላቸው ቀናዒነትና ተቆርቋሪነት የተነሣም የኢትዮጵያ ወጣት ተመራማሪዎችን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ሕይወት ዲፓርትመንት ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ስዊዲን ልከው እንዲማሩ አስደርገዋል።

ዕፀዋትና ደኖች የሕይወት እስትንፋሶች፣ የደስታ ምንጮችና የተፈጥሮ ውበት መናኸሪያዎች፣ የእድገት ምልክቶችና የሕልውና መሠረቶች ስለሆኑ በአሁኑ ሰዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ ሀገራችን አረንጓዴ ካባ እንድትለብስና የድርቅን መቅሰፍት እስከመጨረሻው ተቋቁማ እንድታስወግድ በሚሊዮን የሚገመቱ ችግኞች በየተራራውና በየጋራው፣ በየሜዳውና በየጥጋጥጉ እንዲተከሉ መደረጉና እንክብካቤም ለማድረግ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑ ዶክተር ተወልደ ብርሃንን ጨምሮ በዘርፉ የተሰለፉ ባለሙያዎችንና ቅን ዜጎችን ሁሉ የሚያስደስት ነው። ለምሳሌ፡- ቻይናን ጨምሮ በርካታ ሀገሮች በኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱት የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ስለሚያደርጉ ነው።

**መምህር!**

ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል የቀረበላቸውን ርዕስ ጉዳይ እየተከታተሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሾቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

- ❖ የብዝኃ ሕይወት ጥበቃን በተመለከተ ምን ተረዳችሁ?
- ❖ የተፈጥሮ ሃብትን መጠበቅና መንከባከብ ምን አይነት ጠቀሜታ የሚኖረው ይመስላችኋል?

ቻይናውያን ከከተማ እስከ ገጠር የተፈጥሮ ሀብታቸውን ጠብቀው ይኖራሉ፡፡ በዚህም በቻይና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፤ እንክብካቤ አያያዝ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ይታያል፡፡ የቻይና ተራራ በደን፤ ሜዳና ረባዳው በአዝርዕት፣ በአትክልትና በፍራፍሬ የተሸፈነ በመሆኑ ሁልጊዜ አረንጓዴ ነው፡፡ በአብዛኛው የቻይና ሜዳ ውሃ ገብ በመሆኑ በሩዝ ሰብል፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ተጨናንቆ ሲታይ ለመንፈስ እርካታን ይሰጣል፡፡ በቻይና ያፈጠጠና ያገጠጠ ተራራ፤ ጦም ያደረና የተራቆተ መሬት አይታይም፡፡ በልምላሜ የተዋቡ ተራሮችና ዳገታማ አካባቢዎች በፀሐይ ቃጠሎ እንዳይጠወልጉ፤ አፈራቸው በዝናብና በነፋስ፤ በጎርፍና በማዕበል እንዳይጠራረግ ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ ያደርጋሉ፡፡

ከዚህም የተነሣ፤ የተናደና የተንሸራተተ መሬት፤ ያፈጠጠና ያገጠጠ ተራራ፤ የተራቆተ ዳገትና በወራጅ ውሃ የተጠራረገ አፈር፤ ገደልና ቁልቁለት አይታይም፡፡ ይልቁንም እያንዳንዱ ለምአፈር እንዳይጠረግ በእርከን ሥራ ጋራውና ሸንተረሩ፤ ተራራው፤ ሜዳውና ረባዳው በሽቦና በብረት ሰንሰለት እንደ እሥረኛ ተተብትቦና ተያይዞ አሸዋ ግርፍ ተገርፏል፡፡

ከላይና ከሥር ደግሞ ሐረግና አበባ ተተክሎበት፤ በላዩም ላይ እንደ ሐረግ ዘምቶበት የተለየ የተፈጥሮ ውበት ይታያል። የለመለመውን ሣር፤ የተለያየ ኅብረ ቀለም ያለውን አበባ በየዛፉና በየመንገዱ ዳር ግራና ቀኝ ያስተዋለ ሰው ወደማያውቃትና ልዩ ፕላኔት ወደ ሆነች ምድራዊት ገነት የገባ ያህል ስለሚቆጥረው የተለየ ደስታ ይሰማዋል። ማንም ሕዝብ የሥነ ኑረትን ሕግና ሥርዓት አክብሮ ያለ ስንፍናና ያለ ሌብነት በቅንነት ከሠራ ዓለምን በቀላሉ ሊለውጣት እንደሚችል በ40 ዓመት ውስጥ ተምዘግዝጋ ያደገችው ቻይና እንደ ምሳሌ ልትሆነን ትችላለች። በዚህም ምክንያት ልክ እንደ ዶክተር ተወልደ ሌት ተቀን የሚታክቱ ወገኖቻችንን ፈር ተከትለን ለሀገር መሥራት ደግሞ የእያንዳንዳችን አቢይ ጉዳይ ሊሆን ይገባል።

ዶክተር ተወልደብርሃን በብዝኃ ሕይወት ሀብት አጠባበቅ ላይ በጥልቀት በመሥራታቸውና በተለይም በዓለም አቀፍ ብዝኃ ሕይወት ድርድር ወቅት አፍሪካን ወክለው በጥንካሬና በአንድነት በመቆማቸውና በአዕምሮ ንብረት ጥበቃ ላይ ምርምርና አስተዋጽኦ በማድረጋቸው የተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ መርሐ ግብር (ዩኤፕ) ሚያዝያ 21/1998 ዓ.ም «የምድራችን ጀግና» በሚል በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራትም በርካታ ሽልማቶችን አግኝተዋል።

(አዲስ ዘመን ሐምሌ 28/2011ዓ.ም፣ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ድህረ ማዳመጥ

**መምህር!**

በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በጽሑፍ በማሰራት የተማሪዎቹን የአዳምጦ መረዳት ደረጃ ይፈትሹ፡፡

## ክፍል ሁለት መናገር

**መምህር!**

- የንግግርን መመሪያ በተመለከተ አጭር ማስታወሻ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎቹ እንዲገለብጡ ያድርጉ፡፡
- በመቀጠልም ተማሪዎች  የአጭር ልቦለድ አላባውያንን በተመለከተ አንዱ ተማሪ ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ ደስ ያለውን የቡድን አባል እንዲናገር እድል በመስጠት ተራ በተራ እየተቀባበሉ ያላቸውን ሃሳብ በቃል እንዲገልፁ ያድርጓቸው፤
- ሁሉም የቡድኑ አባላት ተሳታፊ መሆን እንደሚኖርባቸው መመሪያ ይስጧቸው፡፡
- በመጨረሻም ከየቡድኑ አንድ አንድ ተወካይ ተማሪ በመነሳት ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ምዘና

- የንግግርን መመሪያ በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- መመሪያ በመሰጣጣት ሀሳባቸውን መግለፅ መቻላቸውን መገምገም፤
- ሁሉም ተማሪዎች መሳተፋቸውን መዳሰስ፤
- በተወካያቸው አማካኝነት ያቀረቡትን ሀሳብ መገምገም

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

## የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

መምህር!

- ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት መማሪያ መጽሐፉ ላይ ያሉትን የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች በማቅረብ በውይይት እንዲሳተፉና እንዲነቃቁ ያድርጉ፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- ተማሪዎች ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡
- ንብቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ ምክንያታዊ ሆነው መልሳቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤
- በመጨረሻም እርማት ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- አንብበው መገንዘብ መቻላቸውን መፈተሽ፤
- ካነበቡት ጽሑፍ ምን እንደተገነዘቡ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በማሰራት መገምገም፤

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

፩. እውነት

፪. እውነት

፫. ሀሰት

፬. እውነት

፭. እውነት

**ክፍል አራት፡- መጻፍ**

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- በቅድሚያ ተማሪዎች ገላጭ ድርሰትን በተመለከተ አጭር ማስታዎሻ እንዲይዙ ያድርጓቸው፡፡
- መጽሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ያስረዷቸው፡፡
- በመቀጠልም የሰው ልጅ ከልደት እስከሞት የሚያልፍባቸውን ሂደቶች በቅደም ተከተል ገለፃዊ በሆነ መንገድ እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- የፃፉትን ጽሑፍ ዕርስ በዕርስ በመቀያየር ከገላጭ ጽሑፍ ቅርፅ አንፃር እንዲገማገሙ ይዘዟቸው፡፡
- በመጨረሻም ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው በማድረግ ግብረመልስ ይስጧቸው፤ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ገላጭ ድርሰትን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መፃፋቸውን መፈተሽ፤
- አንቀፅ ፅፈው እርስ በእርስ መገማገም መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- ከገላጭ ጽሑፍ አንፃር የፃፉትን አንቀፅ መገምገም፤

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- በቅድሚያ ተማሪዎች ምዕራፍ አምስት ላይ የተማሩትን የእማሬያዊ እና ፍካሬያዊ ፍችን ምንነት ምሳሌ በመስራት እንዲያስታውሱ ያድርጓቸው፡፡
- በመቀጠልም የቀረቡላቸውን ቃላት ተጠቅመው እማሬያዊ እና ፍካሬያዊ ፍችን ማሳየት የሚችሉ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
- በመጨረሻም ግብረመልስም ይስጧቸው፤ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች በተመለከተ ማስታዎስ መቻላቸውን መፈተሽ፤
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር መፃፋቸውን ማረጋገጥ፤

**መልመጃ አንድ**

**በምሳሌው መሰረት የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ አረፍተ ነገር ሰርታች ሁ አመልክቱ፡፡**

፩. መሬት-- መሬት እህል ታበቅላለች፡፡

ዳንቺሴ መሬት ናት፡፡

፪. ምስጥ--- ምስጥ የበላው አዝርዕት ይደርቃል፡፡

ቆጭቶ ምስጥ ነው፡፡

፫. ጉቶ-- የጽድ ጉቶ አያቆጠቁጥም፡፡

ኬሮ ጉቶ ነው፡፡

፬. እርጥብ-- ቡሎ እርጥብ ሳር እያጨደ ነው፡፡

ራዚቃ እርጥብ ናት፡፡

፭. ምላጭ--- ጥፍሬን ልቆርጥ ምላጭ ገዛሁ፡፡

የጀማል አባት ማንንም ማታለል የሚችል ምላጭ ነው፡፡

፮. እሳት --- እሳት ምግብ ለማብሰል ያገለግላል፡፡

ቡንጡ በትምህርቱ እሳት ነው፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ✓ የዓረፍተ ነገር አይነቶችን በተመለከተ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በምሳሌ አስደግፈውም መጠነኛ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- ✓ የቀረቡላቸውን ዓረፍተነገሮች አይነት እንዲለዩ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ የዓረፍተ ነገር አይነቶችን የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱ ትዕዛዝ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- የዓረፍተ ነገር አይነቶችን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤
- የቀረቡላቸውን ዓረፍተ ነገሮች አይነት መለየት መቻላቸውን መገምገም፤
- የዓረፍተ ነገርን አገልግሎት የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች መመስረት መቻላቸውን መፈተሽ፤

**መልመጃ አንድ**

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ጥያቄያዊ፣ ትዕዛዛዊ፣ ሀተታዊ እና አጋናኝ በማለት መልሱ።

ሀ. ሀተታዊ (አዎንታዊ) ዓረፍተ ነገር

ለ. ትዕዛዛዊ ዓረፍ ተነገር

ሐ. ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር

መ. ሀተታዊ (አሉታዊ) ዓረፍተ ነገር

ሠ. ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር

ረ. ሀተታዊ (አሉታዊ) ዓረፍተ ነገር

ሰ. አጋናኝ ዓረፍ ተነገር

# ምዕራፍ ሰባት

# የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ

**(ክፍለ ጊዜ 9)**

**የምዕራፉ አላማዎች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- መረጃ ሰጪ ጽሑፍን በትኩረት አዳምጠው ተግባራዊ ያደርጋሉ፤
- የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምንነት እና የሚያስከትለውን ውጤት ይገልጻሉ፤
- በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ፤
- የአረፍተ ነገሮችን ትዕዛዝ ያነጻጽራሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- በአትኩሮት ማዳመጥ
- ከማይታወቁ ሰዎች ጋር መግባባት
- ፈሊጣዊ ንግግር
- በተለያዩ ርዕሶች ላይ የሚዘጋጅ ጽሑፍ
- የቃላት ተቃራኒ ፍች
- ዓረፍተ ነገር

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛና ሕገ ወጥ ዝውውር በከተማችን

### የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

**"የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛና ሕገ ወጥ ዝውውር በከተማችን"** የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎችዎ ከማንበብዎ በፊት፡-

- በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- ምንባቡን በዝግታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በመቀጠልም ምንባቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- በትኩረት እንዲከታተሉዎት ምክር ይለግሷቸው፡፡
- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸውም ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- ✓ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ሲሰሩ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ምንባቡን እየደጋገሙ በማንበብ የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርሶ መሪነት በቃላቸው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡
- ✓ ለሚሰጡት መልስ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- ካዳመጡት ምንባብ ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በማሰራት የተገነዘቡትን መገምገም፤
- ሁሉም ተማሪዎች የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን መስራት መቻላቸውን መቃኘት፤

## የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛና ሕገ ወጥ ዝውውር በከተማችን

ሕጻናት ከአካላዊና ከአዕምሯዊ እድገታቸው ጋር የተስተካከለና የዕድሜ ደረጃቸውን የሚመጥን የትምህርት መርሃ ግብር የሚያስፈልጋቸው ሲሆን ከወላጆቻቸው ፍቅርና እንክብካቤ በማግኘት በመልካም ስነ ምግባር ታንጸው ማደግ እንደሚገባቸው በህጻናት መብት ድንጋጌዎች ላይ ተቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ በየዕለቱ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች፣ በርካታ ሕጻናት በተለያዩ ምክንያቶች ለጉልበት ብዝበዛና ለሕገ ወጥ ዝውውር እንደተዳረጉ ሲዘገብ እንሰማለን፡፡

ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ሕጻናት በአቅማቸው ምን ዓይነት ስራ መስራት እንዳለባቸው ባለመገንዘብ በአካላቸው፣ በአዕምሯቸውና በስነ ልቦናቸው የሚደርስባቸውን ጉዳት ሳያስቡ፣ እራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ እንደሚጥሩ የተለያዩ ሰነዶች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ለሕጻናት ጉልበት ብዝበዛና ለሕገ ወጥ ዝውውር  ዋናው መንስኤ የወላጆች ወይም የአሳዳጊዎች የግንዛቤ እጥረትና ድህነት መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ከፆታዊ ጥቃት፣ ከሕገ ወጥ ዝውውር፣ ከወሲብ ንግድና ከመሳሰሉት ወንጀሎች ጋር የሚያያዝ በመሆኑ ችግሩ ስር ሰዶ እንዲቆይና ውስብስብ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

የቤተሰቦቻቸውን ድጋፍና እንክብካቤ ያላገኙ በርካታ ሕጻናት ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለሽመና ስራ፣ ለሸክም ስራ፣ ለድንጋይ ጠረባ፣ ለጫማ ጽዳት፣ ለሱቅ ሰራተኝነት፣ ለቤት ሰራተኝነት፣ ለአስተናጋጅነት፣ ለሴተኛ አዳሪነት፣ ለመኪና እጥበት፣ ለሎተሪ አዟሪነት፣ ለመላላክ፣ ለጋራዥ ስራና ለሌሎች መሰል ተግባራት ወደ አዲስአበባ ከተማ በሕገወጥ መንገድ ሲፈልሱ ይታያሉ፡፡ ድርጊቱ ከአካባቢ አካባቢ የችግሩ ስፋትና ጥልቀት  ይለያይ ካልሆነ በስተቀር በሁሉም አካባቢዎች የሚታይ ክስተት ነው፡፡

**መምህር!**

ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ እየተከታተሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሾቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

- በህገ ወጥ መንገድ ከተለያዩ አካባቢዎች ወደአዲስ አበባ የሚመጡ ህጻናት የሚሰማሩባቸው የስራ መስኮች ምን ምን ናቸው?
- ህፃናትን ለህገወጥ ዝውውርና ለጉልበት ብዝበዛ የሚዳርጓቸው ምክንያቶች ምን ምን ይመስላችኋል?

ሕጻናትን ለጉልበት ብዝበዛና ለህገ ወጥ ዝውውር የሚዳርጉ መንስኤዎችን በተመለከተ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሕጻናት መርጃ ማህበር እ.ኤ.አ በ2000 ባወጣው ሪፖርት መሰረት ረሃብ፣ ድርቅ፣ በአካባቢ የሚከሰቱ ግጭቶች፣ በከተማ የአኗኗር ሕይወት መሳብና የመሳሰሉት እንደሆኑ አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪም ወላጆችን በሞት ማጣት እና በህይዎት እያሉም ቢሆን የሚያሳድሩባቸው ተጽዕኖዎች ለሕጻናት ፍልሰትና ህገ ወጥ ዝውውር በምክንያትነት ተጠቅሰዋል፡፡

በሌላ በኩል የኢንዱስትሪዎች በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋት ለሕጻናት ጉልበት ብዝበዛና ለህገ ወጥ ዝውውር በር ከፋች ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም የአብሮ አደግ ጓደኞች ምክርና ቅስቀሳ፣ አላስፈላጊ የሆኑ ቅጣቶች፣ የቤተሰብ ቁጥር መጨመርና የተለያዩ ግጭቶች ሕጻናትን ለጉልበት ብዝበዛ፣ ለጤና ችግርና የተሻለ ኑሮ ፍለጋ በሚል ሰበብ ለህገወጥ ዝውውር እንዲጋለጡ አድርገዋቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ ሕጻናትን በሕገ ወጥ መንገድ በመውሰድና በማዘዋወር ገንዘብ በሚሰበስቡ

ስግብግብ የሰው ነጋዴዎች አማካኝነት በቤት ሰራተኝነት፣ በሕጻናት ሞግዚትነትና በልመና ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ ሆነዋል፡፡

እነዚህ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛና ሕገ ወጥ ዝውውሮች፣ የሚያስከትሏቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች ቀላል የሚባሉ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም በህጻናቱ ላይ አካላዊ፣ አዕምሯዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳት ከማድረሳቸውም በላይ ገለልተኛና ብቸኛ እንዲሆኑ፣ ሀሳባቸውን ለመግለጽ ድፍረት እንዲያጡ፣ ለአካል ጉዳተኝነትና ላለመረጋጋትና እንዲዳረጉ፣ ለመንፈስ ጭንቀት ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል፡፡ በተጨማሪም ሕጻናቱ የወንጀለኛ ተባባሪና ተዋናይ በመሆን ለተለያዩ ሱሶች የተጋለጡ፣ ለህብረተሰብ ባህሎችና ዕሴቶች ክብር የማይሰጡ፣ ለከፍተኛ የጤና ችግሮች የተጋለጡ፣ በትምህርታቸው ደካማ ውጤት የሚያስመዘግቡና የሥነ ምግባር ችግር የሚታይባቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

(በአ/አ/ከ/አ/ት/ቢሮ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛና ህገወጥ ዝውውርን ለመከላከል ከተዘጋጀ መጽሐፈ እድ፤ 2007 ዓ.ም፤ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ድህረ ማዳመጥ

**መምህር! -**

በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በጽሑፍ በማሰራት የተማሪዎቹን የአዳምጦ መረዳት ደረጃ ይፈትሹ፡፡

### መልመጃ ሁለት

**በ "ሀ" አምድስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ"አምድ ስር ካሉት ፍችዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

፩. ሠ

፪. ሰ

፫. መ

፬. ሀ

፭. ረ

፮ ለ

፯. ሐ

## ክፍል ሁለት መናገር

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ❖ ተማሪዎች አራት አባላት ያለው ቡድን መስርተው በቀረቡላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
- ❖ ቡድኑ በተቻለ መጠን የፆታ ስብጥር እንዲኖረው ያድርጉ፡፡
- ❖ በውይይቱ ሁሉም ተማሪዎች መሳተፍ እንደሚኖርባቸው መመሪያ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በመቀጠልም ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ በተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- ❖ በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፤ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ❖ አራት አባላት ያለው ቡድን መመስረታቸውን መፈተሽ፤
- ❖ የተመሰረተው ቡድን የፆታ ስብጥር እንዳለው መቃኘት፤
- ❖ ሁሉም ተማሪዎች ሀሳባቸውን በመግለፅ መሳተፋቸውን መገምገም፤

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ቅድመ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት መማሪያ መጽሐፉ ላይ ያሉትን የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች በማቅረብ በውይይት እንዲሳተፉና እንዲነቃቁ ያድርጉ፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- ተማሪዎች ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡
- ንብቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ ምክንያታዊ ሆነው መልሳቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች በማውጣት ፍች እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡

- በመጨረሻም እርማት ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- አንብበው መገንዘብ መቻላቸውን መፈተሽ፤
- ካነበቡት ጽሑፍ ምን እንደተገነዘቡ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በማሰራት መገምገም፤
- ከምንባቡ ውስጥ ፊሊጦችን አውጥተው ፍች መስጠታቸውን መፈተሽ፤

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉት ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

፩. ሀሰት

፪. ሀሰት

፫. እውነት

፬. እውነት

፭. እውነት

፮. ሀሰት

**መልመጃ ሁለት**

**በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍች የሚሆኑትን ምረጡ።**

፩. ለ ፯. ሀ

፪. ሀ ፯. መ

፫. መ ፰. ለ

፬. ሐ ፱. መ

፭. ሐ ፲. ሀ

**መልመጃ ሶስት**

**በምንባቡ ውስጥ የገቡ ፈሊጣዊ ንግግሮችን በመፈለግ ትርጉማቸውን ጻፉ።**

፩. ልበ ገር--------------------------የዋህ

፪. ሆድ ብሷት----------------------ከፍቷት

፫. አድሮ ቃሪያ----------------------የማይለወጥ

4. ነውር ጌጡ-----------------------ልክስክስ፣ ይሉኝታ ቢስ

5. ከሰውነት ጎዳና ወጣች-----------ከሳች፣ ተጎሳቆለች፣ መነመነች

6. ሰማይ ተደፋባት--------------------ጨነቃት

**መልመጃ አራት**

**በ "ሀ" አምድ ስር ላሉ ፈሊጣዊ አነጋገሮች በ "ለ" አምድ ስር ካሉት ፍቾቻቸው ጋር አዛምዱ።**

፩. ሠ ፫. ሰ

፪. ረ ፬. ሀ

፫. ለ  ፰. ቀ

፬. ሐ  ፱. በ

፯. ሸ  ፲. መ

**ክፍል አራት፡- መጻፍ**

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- በመጀመሪያ ተጀምረው ሳያልቁ የቀረቡላቸውን አንቀፆች ሃሳባቸውን ሳይለቁ እንዲጨርሷቸው ያድርጉ፡፡
- በመቀጠልም ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያበረታቷቸው፡፡
- የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ በህፃናት ላይ የሚያስከትለውን ችግር በተመለከተ አንቀፅ ፅፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡
- በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፤ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ጅምር አንቀፆች ሀሳባቸውን ሳይለቁ መጨረስ መቻላቸውን መፈተሽ፤
- በተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሀሳብ አመንጭተው አንቀፅ መፃፋቸውን ማረጋገጥ፤

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

**መምህር!**

- በቅድሚያ ተማሪዎች የተቃራኒ ቃላትን ምንነት እንዲገነዘቡ በምሳሌ አስደግፈው ያስረዷቸው፡፡
- በመቀጠልም የቃላትን ተቃራኒ በተመለከተ የቀረቡላቸውን ተግባራት እንደአጠያየቅ ባህርያቸው እንዲሰሯቸው ይዘዟቸው፡፡
- በመጨረሻም ግብረመልስም ይስጧቸው፤ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- የቃላትን ተቃራኒ ፍች በተመለከተ ምን እንደሚያውቁ መፈተሽ፤
- የቃላትን ተቃራኒ ፍች በተመለከተ የቀረቡላቸውን ተግባራት መስራት

**መልመጃ አንድ**

**ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል በመምረጥ መልሱ፡፡**

፩. ሐ

፪. ሀ

፫. ለ

፬. ሀ

፭. መ

፮. ለ

፯. መ

፰. ሀ

፱. ሐ

፲. መ

**መልመጃ ሁለት፡-**

**ከታች በዓረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተቃራኒ ፍች የሚሆኑትን ከሰንጠረዡ እየመረጣችሁ ተኩ፡፡**

፩. ንፉግ

፪. ወረዛ

፫. ተጎጂ

፬. ያፋጥናሉ

፭. ምድረ በዳ

፮. መቀራረብ

፯. ዕኩይ

፰. ጥብቅ

**መልመጃ ሶስት፡-**

**በየተራቁጥሩ ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል ልዩ የሆነውን ምረጡ፡፡**

፩. መ

፪. ለ

፫. ሀ

፬. ሐ

፭. ሐ

፮. ለ

፯. መ

፰. ሀ

፱. መ

፲. ሀ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

**መምህር!**

- ✓ የዓረፍተ ነገር አይነቶችን በተመለከተ ምዕራፍ ስድስት ላይ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያድርጓቸው፤
- ✓ በምሳሌ አስደግፈው መጠነኛ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- ✓ የቀረቡላቸውን ዓረፍተ ነገሮች አይነት እንዲለዩ ያበረታቷቸው፤
- ✓ የዓረፍተ ነገር አይነቶችን ከአገልግሎታቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያግዟቸው፤
- ✓ በመጨረሻም ግበረመልስ ይስጧቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- የቀረቡላቸውን ዓረፍተ ነገሮች አይነት መለየት መቻላቸውን መገምገም፤
- ዓረፍተ ነገሮችን ከአገልግሎታቸው ጋር ማዛመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ፤

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ሀተታዊ (አሉታዊ፣ አዎንታዊ)፣ ትዕዛዛዊ፣ እና መጠይቃዊ በማለት መልሱ።**

፩. መጠይቃዊ

፪. ሀተታዊ (አዎንታዊ)

፫. ትዕዛዛዊ

፬. መጠይቃዊ

፭. ትዕዛዛዊ

፮. መጠይቃዊ

፯. ሀተታዊ (አዎንታዊ)

፰. ሀተታዊ (አሉታዊ)

፱. ትዕዛዛዊ

፲. ሀተታዊ (አዎንታዊ)

**መልመጃ ሁለት**

**በ "ሀ" አምድ ያሉትን የዓረፍ ተነገር አይነቶች በ "ለ" አምድ ካለው አገልግሎታቸው ጋር አዛምዱ።**

፬. ሐ

፭. መ

፮. ለ

፯. ሀ

# ምዕራፍ ስምንት

# ሰላም

(ክፍለ ጊዜ 9)

**የምዕራፉ አላማዎች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- አዳምጠው ጽሑፉን ይተነትናሉ፤
- የሰላምን አስፈላጊነት ይገልፃሉ፤
- አንብበው የጽሑፉን ሀሳብ በማጠቃለል ይጽፋሉ፤
- በጽሑፍ ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ይጠቀማሉ፤

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ✓ አዳምጦ መተንተን
- ✓ ሀሳብን እንደገና መከለስ
- ✓ አንብቦ ሀሳቡን ማጠቃለል
- ✓ ሥርዓተ ነጥብ
- ✓ የተለመዱ ቃላት
- ✓ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር



## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ሰላምን ፍለጋ

### የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

" **ሰላምን ፍለጋ** " የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎችዎ ከማንበብዎ በፊት፡-

- በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- ምንባቡን በዝግታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- የምንባቡን ሀሳብ መረዳት እስኪችሉ ድረስ ድምፅዎን ከፍ እያደረጉ ያንብቡላቸው፡፡
- በመቀጠልም ምንባቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- በትኩረት እንዲከታተሉዎት ምክር ይለግሷቸው፡፡
- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸውም ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸውም ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- ✓ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ በመቀጠልም ምንባቡን እየደጋገሙ በማንበብ የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርሶ መሪነት በቃላቸው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡
- ✓ ለሚሰጡት መልስ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- ካዳመጡት ምንባብ ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በማሰራት የተገነዘቡትን መገምገም፤
- ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄ በመመለስ መሳተፋቸውን መፈተሽ፤

## ሰላምን ፍለጋ

ሰላም በየትኛውም መልኩና በማንኛውም ጊዜ ሰላምን ሊያውኩ ከሚችሉ ሁከትና ሌሎች ተግባራት፣ ከስጋትና የሰቀቀን ህይወት ሙሉ በሙሉ ነፃ ሆኖ መኖር ነው፡፡ በሰላም ለመኖር ደግሞ ከጦርነት፣ ከሁከት፣ ከግጭትና ከብጥብጥ ወዘተ. ነፃ የሆነ አካባቢ ያስፈልጋል፡፡ በማንኛውም መንገድ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ አብሮ ለመኖር ካስፈለገ መተሳሰብ፣ መደጋገፍ፣ መወያየትና መቻቻል እጅግ ወሳኝ ተግባራት ናቸው፡፡ ሰላም የባህሪ፣ የአመለካከት፣ የአኗኗር ወዘተ. እሴቶች ስብስብ ነው፡፡ ስለዚህ ሰላም ከጦርነት፣ ከአመፅ፣ ከሽብር፣ ከሁከት፣ ከብጥብጥና

ከመሳሰሉት ተግባራት አንፃር እራስን በማራቅ ግጭቶችን ሁሉ በውይይትና በመግባባት ለመፍታት የሚያስችል መሳሪያ ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት የሰው ዘር በሙሉ ሰላምን በመፈለግ ላይ ነዉ፡፡ ስለ ሰላም ብዙዎች ዘምረዋል፤ በርካቶችም አዚመዋል፡፡ ስለ ሰላም ጥቂት የማይባሉ ደራስያን ጽፈዋል፤ አያሌዎችም ህይወታቸውን የመስዋዕት በግ አድርገዋል፡፡ ሰላምን ፍለጋ አያሌዎች መንፈሳዊ ጉዞዎች አድርገዋል፡፡ በአንጻሩ ሌሎች ደግሞ ሰላምን ሲፈልጉ በተስፋ መቁረጥ የሱስ ተጋላጭ በመሆን የነበራቸውን አንፃራዊ ሰላማቸውን አጥተው በመንገድ ላይ ወድቀው ቀርተዋል፡፡ አልያም ለዘላለም ሰላም ወደሌለበት ተሸጋግረዋል፡፡ ሚሊዬኖችም ሰላምን ለመሻት ከአገር ከቀያቸው ተሰደዉ በየሰዉ አገራት ተንከራተዋል፤ የሰዉነትንም ስብዕናና ክብር አጥተዋል፡፡

ወላጆች ደግሞ የልጆቻቸውን ስም ሰላም፣ ሰላማዊት፣ ሰላሙ፣ ፍቅረ ሰላም ወዘተ. ብለዋል፡፡ ከተሞችም ሀገረ ሰላም፣ ፍኖተሰላም፣ ሰፈረ ሰላም ተብለዋል፡፡ የአምልኮ ስፍራዎችም ደጀ ሰላም፣ ደብረሰላም በመባል የሰላም ምኞት መግለጫ ሆነዋል፡፡ በዓለም አደባባዮች አያሌ መንግስታትና ሀገራት የሰላም ማስጠበቅ ስምምነት ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡ ነገር ግን ገና ፊርማቸው ሳይደርቅ ለግጭት የተጋበዙ፣ የአደራዳሪና አስታራቂ ሽማግሌ የጠሩ በርካቶች ናቸው፡፡ በአንዳንድ ሀገራት ጉንጭ ማልፋት ቢሆንም ቅሉ ሰላምን ለማጽናት በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

**መምህር!**

ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ እየተከታተሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሾቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

- ሰላምን በተመለከተ እስካሁን የተረዳችሁት ምንድን ነው?
- ሰላም በአንድ ወገን ጥረት እውን የሚሆን ይመስላችኋል? እንዴት?

ለሰላም መታሰቢያነት አርማዎች በዕርግብ ምስል ከአገራት ባንዲራ ጎን ለጎን ተውለውልበዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሰላም መጥፋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ የሰላም መደፍረስ መነሻ ምክንያቱ ከወትሮው ቀላል ለመፍታት ግን ዉስብስብና አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል፡፡ አሁን አሁን ሰላምን ከማግኘት ይልቅ ሰላምን ማጣት ለሰው ልጆች ቀላል እየሆነ ነው፡፡ የሰው ልጅ በምድር እየበዛ በመሄዱ ምክንያት የሀጢያት መረብ ከመቼውም በላይ ውስብስብና ለመበጠስ አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል፡፡

ዓለም ከዬትኛውም ጊዜ ይልቅ በሰላም እጦት ምክንያት እየተናወጠች ያለችበት ጊዜ ላይ እንገኛለን፡፡ መላው ዓለም ያለ ልዩነት በሚባል ሁኔታ በነውጥና በግጭት ውስጥ ነው፡፡ ፍጥረት በሙሉ በሰዉ ልጆች ሰላም ማጣት ዋጋ እየከፈለ ነዉ፡፡ በተቃራኒው በሰዉ ልጆች ታሪክ ሰዎች ሁሉ ያለልዩነት ሰላምን የሚፈልጉበት ወቅትም ነው፡፡ በመሰረቱ ሰላምን ማስጠበቅ የአንድ ወገን የቤትስራ አይደለም፡፡ ይልቁን ሰላም የእያንዳንዱን ግለሰብ በጎ ፈቃድና ትብብር የሚጠይቅ ነገር ነዉ፡፡

ሰላምን መፈለግ ብቻውን ሰላምን አያስገኝም፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ግለሰብ እራሱን የሰላም አለቃ፣ ለሰላም ዘብ ቋሚ አድርጎ በመሾም የሚጠበቅበትን ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በመጀመሪያ ራሱን ሰላም ማድረግ፣ ከዚያ

አካባቢውን ሰላም ማድረግ፣ ሲቀጥልም የሀገሩን ሰላም መጠበቅና ማስጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ሰላምን ለማግኘት ቀላ መውረድ፣ ደጋ መውጣት አይጠበቅም፡፡ ብዙ መመራመርና ማሰብም አያስፈልግም፡፡ ምክንያቱም ሰላም ያለው ከእያንዳንዱ ግለሰብ ውስጥ ነውና፡፡ የራሱን ሰላም መጠበቅ የቻለ ዜጋ ሌላውን ለመበጥበጥ አይነሳሳም፤ በተቃራኒው ከራሱ ጋር ሰላምን ያላወረደ ሰው ደግሞ ሌላውን ሰላም ሊሰጥ አይችልም፡፡ ስለዚህ ሰዎች ሰላምን ፍለጋ ከመንከራተት ይልቅ ከራሳቸው ጋር መታረቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህ ተግባራዊነት ደግሞ ቅንነት፣ ታማኝነትና የዓላማ ፅናት እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

| |
|---|
| ***መምህር!***<br>በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በጽሑፍ በማሰራት የተማሪዎቹን የአዳምጦ መረዳት ደረጃ ይፈትሹ፡፡ |

***መልመጃ አንድ፡-***

***ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡***

፩. ሀሰት

፪. ሀሰት

፫. እውነት

፬. ሀሰት

፭. እውነት

፮. ሀሰት

**መልመጃ ሁለት፡-**

**ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

፩. መ　　　　፬. መ

፪. ሐ　　　　፭. ሀ

፫. ለ　　　　፮. ለ

**ክፍል ሁለት መናገር**

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

መምህር!

- ❖ ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ ሆነው በቀረቡላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
- ✓ በተቻለ መጠን ፆታዊ ስብጥር እንዲኖር ያድርጉ
- ❖ በውይይቱ ሁለቱም ተማሪዎች መሳተፍ እንደሚኖርባቸው መመሪያ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በመቀጠልም ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ በተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- ❖ በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፤
- ❖ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

ምዘና

- ❖ ጥንድ ጥንድ ሆነው ለመወያየት መዘጋጀታቸውን መዳሰስ፤
- ✓ ሴትና ወንድ መሆናቸውን መፈተሽ፤
- ❖ ሁለቱም ተማሪዎች ሀሳባቸውን በመግለፅ መሳተፋቸውን መገምገም፤
- ❖ በውይይቱ የመናገር ክሂላቸውን መገምገም፤

**ክፍል ሶስት፡- ማንበብ**

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ቅድመ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

*መምህር!*

- ❖ ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት መማሪያ መፅሃፉ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በማቅረብ በውይይት እንዲሳተፉና እንዲነቃቁ ያድርጉ፡፡
- ❖ በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ቀስ አድርገው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፤
- ✓ በተጨማሪም መማሪያ መፅሀፉ ላይ የቀረበውን ስዕል ጓደኞቻቸው እንዲገልፁላቸው ይዘዟቸው፡፡
- ❖ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡
- ✓ መስማት መቻል አለመቻላቸውን በመጠየቅ መስማት እስኪችሉ ድረስ ድምፅዎትን ከፍ አድርገው ያንብቡላቸው፡፡

**ጊዜ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- ❖ ተማሪዎቹ ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ከዚያ አንድ ፈቃደኛ ተማሪ ተነስቶ ድምፁን እያሰማ ክፍል ውስጥ ላሉት ተማሪዎች እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡
- ❖ ንባቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ሰላም በሚል በቀረበው ግጥም ውስጥ ያሉትን ቃላት ሀሳብ መመርመር

እንዲችሉ ያግዟቸው፡፡

- መረዳት እስኪችሉ ድረስም ደጋግመው እንዲያነቡት መመሪያ ይስጧቸው፡፡
- አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው በማንበብ እንዲተባበሯቸው የማግባባት ስራ ይስሩ፡፡
- መስማት የተሳናቸውን ተማሪዎች ደግሞ ወደፊት መጥተው እንዲቀመጡ በማድረግ መስማት እስኪችሉ ድረስ ድምፅ በመጨመር እንዲነበብላቸው ያድርጉ፡፡

**ድህረ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ በተቻለ መጠን ተማሪዎች ምክንያታዊ ሆነው መልሳቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤
- ✓ ለሚሰጡት መልስም እርማት ይስጧቸው፡፡
- በመቀጠልም በቃላቸው ሽምድደው ለጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፤ ያበረታቷቸውም፡፡
- ከዚህ በፊት የመሳተፍ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች እድል ቅድሚያ በመስጠት እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- አንብበው መገንዘብ መቻላቸውን የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን በማሰራት መፈተሽ፤
- ካነበቡት ፅሁፍ ምን እንደተገነዘቡ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በማሰራት መገምገም፤
- የግጥሙን ሀሳብ መረዳት መቻላቸውን በአንድ አንቀፅ እንዲፅፉት በማድረግ መዳሰስ፤
- የመሳተፍ ችግር የነበረባቸው ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ ማድረግ አለማድረጋቸውን መፈተሽ

**መልመጃ አንድ፡-**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡**

፩. እውነት

፪. ሀሰት

፫. እውነት

፬. ሀሰት

፭. ሀሰት

፮. እውነት

፯. እውነት

፰. ሀሰት

፱. እውነት

፲. እውነት

**መልመጃ ሁለት፡-**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

፩. መ

፪. ሐ

፫. ሀ

፬. መ

፭. መ

፮. ሀ

፯. ለ

**መልመጃ አራት፡-**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በግጥሙ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

፩. ሐ

፪. መ

፫. ለ

፬. መ

፭. መ

፮. ሀ

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

**መምህር!**

- ❖ በመጀመሪያ የስርዓተ ነጥብን ምንነት እና አይነቶች በተመለከተ ከዚህ በታች የቀረበውን ፅሁፍ መሰረት በማድረግ አጭር ማስታዎሻ ያስይዟቸው፤
- ❖ ምሳሌዎችን ተጠቅመውም ግልፅ እንዲሆንላቸው ያድርጉ፡፡
- ❖ በመቀጠልም መማሪያ መፅሀፋቸው ላይ ስርዓተ ነጥብን በተመለከተ የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡
- ❖ አያይዘውም የቀረቡላቸውን ስርዓተ ነጥቦች ተጠቅመው አንቀፁን እንደገና እንዲፅፉ ያግዟቸው፡፡
- ❖ የጻፉት አንቀፅ ሀሳብ ከግጥሙ ሀሳብ ጋር መጣጣም መቻሉን እርስ በዕርስ በመቀያየር እንዲተያዩ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፤
- ❖ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ስርዓተ ነጥብን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- የቀረቡላቸውን ስርዓተ ነጥብ ነክ ጥያቄዎች መስራት መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- የቀረቡላቸውን ስርዓተ ነጥቦች በትክክለኛ ቦታቸው ላይ በማድረግ አንቀፁን እንደገና መፃፋቸውን መገምገም፤

## ሥርዓተ ነጥቦች

በወረቀት ላይ የሰፈረ ሐሳብ (ቋንቋ) መልዕክቱ ግልጽ ሆኖ እንዲተላለፍ ሥርዓተ-ነጥቦች የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ በአብዛኛው አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት ሥርዓተ-ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩. ሁለት ነጥብ ከሠረዝ (፦)

- መሪ ሐሳቡን ተከትለው ወደሚመጡ ዝርዝር ነገሮች ለማንደርደር ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ቋንቋ አራት ክሂሎች አሉት፡፡ እነሱም፦ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ናቸው፡፡

፪. ነጠላ ሠረዝ (፣) ወይም (፥)

የተለያየ አገልግሎት አለው፡፡ እነሱም፡-

ሀ. ተመሳሳይ ሙያ ያላቸውን ተከታታይ ቃላት ለመለየት

ምሳሌ፡- ድርጅታችን ጨው፣ ስኳር፣ ጥራጥሬ፣ ዱቄትና ዘይት ያከፋፍላል፡፡

ለ. በተከታታይ የሚመጡ ንዑስ ሐረጎችን ለመለየት፡፡

ምሳሌ፡- ወረቀት ከዓለማየሁ፣ እርሳስ ከዘውዴ፣ ላጲስ ከጥሩወርቅ ተበድሮ

፫. ድርብ ሠረዝ (፤)

ሀ. ሁለት ሐሳቦችን በመስተፃምር አማካይነት አጣምሮ ለማቅረብ

ምሳሌ:- ልጁን ደጋግሜ መከርኩት፤ ይሁን እንጂ ሊሰማኝና ሊመለስ አልቻለም፡፡

ለ. ተያያዥነት ያላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ ዓረፍተነገሮች አከታትሎ ለማቅረብ

ምሳሌ2፡- ሥራውን በርትቶ ይሠራል፤ያገኘውን በደስታ ይበላል፤በጊዜ ገብቶ ይተኛል፡፡

፬. ሦስት ነጥብ (. . .)

ሀ. ከሌላ ሰው ከተወሰዱት ሐሳቦች ውስጥ የቀሩ ወይም የተዘለሉ መኖራቸውን ለማመልከት

ለ. ተመሳሳይ ነገሮች የሚቀጥሉ መሆናቸውን ለማመልከት። በሌላ አነጋገር ወዘተ. ለማለት ያገለግላል።

ምሳሌ፡- እንደ ወንበር፣ አልጋ፣ ጠረጴዛ... የመሳሰሉትን ብዙ ብር አውጥቶ ገዛ።

፫. ትዕምርተ ጥቅስን (የጥቅስ ምልክትን)

- በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል።

ሀ. ሙሉ የጥቅስ ምልክት (" ")

- የጸሐፊው ሐሳብ አለመሆኑን ለማመልከት ያገለግላል።

ምሳሌ፡- "ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው" ሲባል አልሰማህም?

- አንዳንድ የተውሶ ቃላት በቋንቋው ውስጥ ሲጻፉ ባዕድነታቸውን ለማመልከት ያገለግላል።

ምሳሌ፡- የእግሩ ሕመም መንስኤ የ"ነርቭ" መሸማቀቅ ነው።

- የሁለት ሰዎችን ምልልሳዊ ንግግር ለየብቻ በጥቅስ ቀንብቦ ለማሳየት

ምሳሌ፡- "ዛሬ ትምህርት ቤት ሄደሃል?" "አዎና! ግን ለምን ጠየቅከኝ?" "የትራንስፖርት ችግር ስለነበረ"

፮. ነጠላ የጥቅስ ምልክት (' ')

- አንድ ፀሀፊ ፀሐፊ በጠቀሰው ጥቅስ ውስጥ ሌላ ጥቅስ ካጋጠመው በነጠላ የጥቅስ ምልክት መለየት ይኖርበታል።

ምሳሌ፡- "በርትተን ለመማርና ጥሩ ውጤት ለማምጣት 'ሁልጊዜ ትጉ' የሚለውን

የመምህራችንን ምክር እናስታውስ” በማለት የክፍል አለቃው ጓደኞቹን መከረ።

፮. ትእምርተ-አንክሮ (የቃለ አጋኖ ምልክት) (!)

ይህ ምልክት መገረምንና መደነቅን፣ ግዴታና ትዕዛዝን፣ ማሞካሸትና ማድነቅን፣ ቁጣና ልመናን፣ ጩኸትና ለቅሶን ወዘተ. ለማመልከት ያገለግላል።

ምሳሌ፡-

ጎሽ! አንጀቴን አራስከው!

፯. ትእምርተ-ጥያቄ (የጥያቄ ምልክት) (?)

ምሳሌ፡- የቤት ሥራህን ሠርተሃል?

፱. እዝባር (አቆልቋይ) (/)

- ይሄ ምልክት አንዳንዴ ሲፃፍ መስመር ይባላል።

ሀ. አንድን ቃል በመጀመሪያውና በመጨረሻው ፊደል አሳጥሮ ለመጻፍ

ምሳሌ፡- ወ/ሮ = ወይዘሮ ወ/ር = ወታደር

ለ. የጥምር ቃሉን የመጀመሪያ ፊደል ብቻ አሳጥሮ ለመፃፍ

ምሳሌ፡- ት/ቤት = ትምህርት ቤት፣ ጽ/ቤት = ጽህፈት ቤት

ምሳሌ፡- በዓረፍት ነገር ውስጥ የቃላትን/ የሐረጎችን ትርጉም ማጤን ተገቢ ነው።

ሐ. የመሥሪያ ቤት ደብዳቤ መለያ ቁጥሮችንና ዓመተ ምኅረትን ለመለየት

ምሳሌ፡- ቁጥር 385/ 31/ 2001

**፲. ቅንፍ ( )**

- "ወይም" የሚለውን አማራጭ ቃል ተክቶ እንዲያገለግል ሲፈለግ

ምሳሌ፡- ነገ ጧት ወላጅህን (አሳዳጊህን) ይዘህ መምጣት አለብህ።

## ፲፩. ሠረዝ (ጭረት)

- ❖ ንዑስና ዐቢይ በማለት በሁለት ይከፈላሉ።

ሀ. ንዑስ ሠረዝ (-)

- ➢ ጥምር ቃላትን ለማመልከት

ምሳሌ፡- ቃለ- ጉባዔ፣ ሰው-ሠራሽ

ለ. ዐቢይ ሠረዝ (–)

- ➢ ይህ ሠረዝ "እስከ" የሚለውን ትርጉም ይይዛል።

ምሳሌ፡ -ከአዲስ አበባ – ሰበታ በእግሬ ተጓዝኩ።

## ፲፪. አራት ነጥብ (።)

- ➢ አራት ነጥብ እርግጠኛና ቀጥተኛ የሆኑ ጉዳዮች በዐርፍተ- ነገር ተጽፈው ሙሉ ዕረፍት ሲደረግና ሐሳቡም ሲቋጭ መደምደሚያ ሆኖ ይገባል።

ምሳሌ፡- አስተማሪው ተማሪዎቹን ከልብ ያስተምራል።

(ታሪኩ ፋንታዬ፣ "አማርኛ ሁሉ ለሁሉ" ፳፻፩ ዓ/ም)

**መልመጃ አንድ፡-**

**የሚከተሉትን ስርዓተ ነጥብ ነክ ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው መልስ ስጡ።**

፩. ሐ

፪. ሀ

፫. ለ

፬. መ

፭. ሐ

**መልመጃ ሁለት፡-**

**ከሚከተሉት ስርዓተ ነጥቦች መካከል ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ በአንቀፁ ውስጥ ያሉትን ቁጥሮች ተኩ።**

**ጥያቄ ፩፡-**

፩. ድርብ ትዕምርተ ጥቅስ

፪. ነጠላ ሰረዝ

፫. ድርብ ሰረዝ

፬. ቃለ አጋኖ/ ትዕምርተ አንክሮ

፭. አራት ነጥብ

ጥያቄ ፪፡-

፩. አራት ነጥብ

፪. ድርብ ጥዕምርተ ጥቅስ

፫. ጥያቄ ምልክት

፬. ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ

፭. ነጠላ ሰረዝ

፮. አራት ነጥብ

**መልመጃ ሶስት፡-**

**በ "ሀ" አምድ ስር ላሉ ስርዓተ ነጥቦች በ "ለ" አምድ ስር ካሉት አቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

| | |
|---|---|
| ፩. ሐ | ፮. ሸ |
| ፪. ሠ | ፯. ረ |
| ፫. ሀ | ፰. በ |
| ፬. መ | ፱. ሰ |
| ፭. ቀ | ፲. ተ |

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

**መምህር!**

- በቅድሚያ ተማሪዎች ምዕራፍ አንድ ላይ የተማሩትን የአውዳዊ ፍች ምንነት እንዲያስታውሱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ጥያቄዎችን በማቅረብም መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠልም በዓረፍተነገር ውስጥ ለቀረቡላቸው ቃላት አውዳዊ ፍች እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የሰጡትን ፍች በማየት እርማት ይስጧቸው፡፡
- አያይዘውም የቀረቡላቸውን ቃላት አውዳዊ ፍች ተጠቅመው ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የመሰረቱትን ዓረፍተነገር በማየት እርማት ይስጧቸው፡፡
- በተጨማሪም የመዝገበ ቃላትን ፍች ምንነት በምሳሌ አስደግፈው ያስረዷቸው፡፡
- ✓ መዝገበ ቃላት ተጠቅመው ቃላትን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ የመዝገበቃላት መፅሀፍ ክፍል ይዘው ገብተው ያሳይዋቸው፡፡
- አያይዘውም መማሪያ መፅሀፋቸው ላይ ለቀረቡላቸው ቃላት መዝገበ ቃላት ተጠቅመው ፍች እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡
- በመጨረሻም ግብረመልስም ይስጧቸው፡፡
- ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- የቃላትን አውዳዊ ፍች ምንነት ማስታወስ መቻላቸውን ጥያቄ በመጠየቅ

መገምገም፤

- ለቀረቡላቸው ቃላት አውዳዊ ፍች መስጠታቸውን ማረጋገጥ፤
- አውዳዊ ፍቻቸውን ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር መመስረት መቻላቸውን መፈተሽ፤
- የመዝገበ ቃላዊ ፍችን ምንነት በተመለከተ የሚያውቁትን ነገር መገምገም፤
- መዝገበ ቃላት ተጠቅመው ለቀረቡላቸው ቃላት ፍች መስጠታቸውን መዳሰስ፤

**መልመጃ አንድ፡-**

**በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡**

፩. ተጓዘ፣ ሔደ

፪. መፃፊያውን፣ እስክርቢቶውን

፫. ተናገረች፣ ገለፀች

፬. በአንድነት፣ በጋራ

፭. ተቀያያሪ

፮. የሚደረደሩ

**መልመጃ ሶስት**

**የሚከተሉትን ቃላት መዝገበ ቃላት ተጠቅማችሁ ፍቻቸውን ስጡ፡፡**

፩. አንባቢ፣ አድማጭ፣ ተመልካች

፪. ተጋባዥ፣ ተሳታፊ

፫. ምሳሌነት፣ ፍቱን መድሀኒት

፬. መብራት፣ ብርሀን

፭. ፈረደ፣ ለየ

፮. እንከን፣ ጉድለት

፯. ደሞዝ፣ ክፍያ

፰. መጀመሪያ

፱. ወሰንተኛ፣ ድንበርተኛ

፲. ሥነስርዓት፣ ፀጥታ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

## የትምህርቱ አቀራረብ

## ትዕዛዝ

**መምህር!**

- ✓ በመጀመሪያ የነጠላ ዓረፍተ ነገርንና የውስብስብ ዓረፍተ ነገርን ምንነት በተመለከተ አጭር ማስታወሻ ያስይዟቸው፤
- ✓ ግልፅ እንዲሆንላቸውም በምሳሌ አስደግፈውም ያስረዷቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- ✓ የቀረቡላቸውን ዓረፍተነገሮች ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር እያሉ እንዲለዩ ያድርጓቸው፤
- ✓ አያይዘውም በራሳቸው አምስት አምስት ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍ ተነገር እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**ምዘና**

- ውስብስብና ነጠላ ዓረፍተ ነገርን በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- የቀረቡላቸውን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላና ውስብስብ እያሉ መለየት መቻላቸውን መገምገም፤
- ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መመስረት መቻላቸውን መዳሰስ፤

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር እያላችሁ ለዩ።**

፩. ነጠላ ዓረፍተ ነገር

፪. ውስብስብ ዓረፍ ተነገር

፫. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

፬. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

፭. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

፮. ነጠላ ዓረፍተ ነገር

፯. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

፰. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

፱. ነጠላ ዓረፍተ ነገር

፲. ነጠላ ዓረፍተ ነገር

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## የአየር ንብረት ለውጥ

**(9 ክፍለ ጊዜ)**

***የምዕራፉ አላማዎች፡-*** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የጽሑፉን ሀሳብ አዳምጠው ይገመግማሉ፤
- ስለ አየር ንብረት ለውጥ ምንነት ያብራራሉ፤
- የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ውጤት ያብራራሉ፤
- ለተለያየ አላማ ያነባሉ፡፡

***የምዕራፉ ይዘቶች፡-***

- አዳምጦ መመዘን
- ያልተለመዱ ቃላት
- ለተለያየ አላማ ማንበብ
- ስዕሎችን በጥልቀት መግለጽ
- አውዳዊ ፍች
- ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## የአየር ንብረት ለውጥና የአካባቢ ብክለት

## የትምህርቱ አቀራረብ

***ቅድመ ማዳመጥ***

***ትዕዛዝ***

***መምህር!***

«የአየር ንብረትና የአካባቢ ብክለት» የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎችዎ ከማንበብዎ በፊት፡-

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው ስዕሉን እንዲገልፁላቸው ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

***ጊዜ ማዳመጥ***

***ትዕዛዝ***

- በመቀጠልም ምንባቡን በዝግታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- መስማት መቻል አለመቻላቸውን በመጠየቅ፣ መስማት እስኪችሉ ድረስ ድምፅዎን ከፍ አድርገው ያንብቡላቸው፡፡
- የሚያነቡላቸውን ምንባብ አዳምጠው አጭር ማስታወሻ እንዲይዙ ይዘዟቸው፡፡

- በመቀጠልም ምንባቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- በትኩረት እንዲከታተሉዎት ምክር ይለግሷቸው፡፡
- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸውም ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎችን በጽሑፍ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ለቀረበላቸው ስዕል ጥልቅ ትንታኔ እንዲሰጡ ያለማምዷቸው፡፡
- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸውም ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡
- ✓ ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡
- ✓ ለሚሰጡት መልስ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው ጥያቄዎችን መመለስ መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- ስዕሉን ተመልክተው ጥልቅ ትንታኔ መስጠት መቻላቸውን መቃኘት፤
- ለማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሽ መስጠት መቻላቸውን መገምገም
- ካዳመጡት ምንባብ ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎችን መስራት መቻላቸውን መገምገም፤

# የአየር ንብረት ለውጥና የአካባቢ ብክለት

የሰው ልጅ ከሚኖርበት አካባቢ ጋር ትስስርና ቁርኝት አለው፡፡ ሕይወቱን ለማቆየት ከተፈጥሮ ጋር ትግል ስለሚያደርግ በአካባቢው በሚገኘው የተፈጥሮ ሀብት ይጠቀማል፡፡ የተፈጥሮ ሀብት የምንላቸው ደግሞ በመሬት ላይና ከመሬት ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ በመሬት ላይ እንደ አፈር፣ ውሃና የመሳሰሉትን የሚያካትት ሲሆን በመሬት ውስጥ ደግሞ ልዩ ልዩ ማዕድናትን የሚያጠቃልል ነው፡፡ የሰው ልጅ ከአካባቢው የተፈጥሮ ሀብቶች ጋር ጥብቅ የሆነ ቁርኝት ቢኖረውም አውቆም ይሁን ሳያውቅ ለህልውናው መሰረት በሆኑት የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጉዳት ሲያደርስ ይታያል፡፡ ይህም ጉዳት (ብልሽት) የአካባቢ ብክለት በመባል ይታወቃል፡፡

ዛሬ በተለያየ መልኩ የምናየው የአካባቢ ብክለት የተፈጥሮ አካባቢያችንን እያጠፋና ህልውናችንን እየተፈታተነ ይገኛል፡፡ ይህ ብክለት ብዙ የተለያዩ ነገሮችን የሚያጠቃልል ሲሆን በቀላሉ የምናየውና ጉዳቱንም በቶሎ የምንገነዘበው አይደለም፡፡ ምንም እንኳን በሀገራችን የአየር ብክለት በገጠሩ አካባቢ ብዙ ጎልቶ ባይታይም በትላልቅ ከተሞች ከአውቶቡሶች፣ ከጭነትና ከቤት ተሽከርካሪዎች የሚወጣው መርዛማ ጭስ አካባቢን ሲበክል ይታያል፡፡ በተለይ እንደ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ ናዝሬት፣ ሻሸመኔ፣ መቀሌ፣ ባርዳር፣ አዋሳ፣ ጎንደር የመሳሰሉት ከተሞች ለዚህ ጉዳይ አይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ከፋብሪካ የሚወጣ ጭስም አየርን ለመበከል አይነተኛ አስተዋጽዖ አለው፡፡ እነዚህ ሁሉ ተዳምረው አካባቢያችንን ለመርዛማ የአየር ብክለት ይዳርጉታል፡፡

የአየር ብክለት ከፍተኛውን የፀሀይ ሙቀት መጠን በሚከላከልልን "ኦዞን" ተብሎ በሚታወቀው አየር ላይ እያደረሰ ስላለው ጉዳት ሰምታችሁ ይሆናል፡፡ የአካባቢ ብክለት የኦዞንን ሽፋን እያሳሳ የመሬታችንን የከባቢ አየር ሙቀት መጠን እንዲጨምር አድርጓል፡፡ የዚህ ከፍተኛ የሙቀት መጠን መከሰት በአካባቢያችን አየር ንብረት ላይ ችግር አስከትሏል፤ ቀዝቃዛው አየርም ሸሽቷል፡፡ በዚህም ሳቢያ ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ ስለማይዘንብ እህል በበቂ ሁኔታ አይመረትም፡፡

**መምህር!**

*ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ እየተከታተሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሾቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡*

- *የአየር ብክለት መንስኤዎችን ዘርዝሩ፡፡*
- *ደኖች ያለአግባብ የሚጨፈጨፉ ከሆነ ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?*

በደኖች ያለአግባብ መጨፍጨፍ ምክንያት የካርቦንዳይ ኦክሳይድ በአየር ውስጥ መሰራጨት ሌላው ብክለትን ከሚያደርሱ ሁኔታዎች አንዱ ነው፡፡ የውሃ ብክለትም በቀላሉ የማይታይና በሰውም ሆነ በውሃ ውስጥ በሚኖሩ ፍጥረታት ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ ነው፡፡ ወራጅ ውሃ ወይም ወንዝ በአንዲት ጠብታ መርዝ ከተበከለ በሚያልፍበት አካባቢ ሁሉ የሚገኙ ህይወት ያላቸው ነገሮች (አሳ፣ እንቁራሪት ወዘተ) ነፍሳት በቀላሉ ይሞታሉ፡፡ ምናልትባም ይህንኑ ውሃ ለምግብ ማብሰያና ለመጠጥ የምንጠቀምበት ከሆነም በጤንነታችን ላይ የሚደርሰውን ጉዳት መገመት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡

ሰዎች በየቦታው በሚጸዳዱበት ጊዜ አይነ ምድርና ሽንት በዝናብ እየተጠረገ ወደ ወንዞች ይገባሉ፡፡ የወንዝ ውሃ ለማብሰያ ወይም ለመጠጥ የሚውል ከሆነ ውሃ ውስጥ በሚፈጠሩት ጠንቀኛ ጀርሞች ሳቢያ እንደ ቢልሃርዚያ፣ ኮሌራ፣ የተስቦ በሽታና ሌሎች ጠንቆች ያጋጥሙናል፡፡ ምናልባትም መጸዳጃ ቤቶች ቢኖሩም እንኳን ከውስጣቸው እየሰረገ በሚከሰተው የውሃ ብክለት ከፍተኛ የጤንነት ችግር ይደርሳል፡፡

የቤት ዕቃዎችንና ልብሶችን ወራጅ ውሃ ውስጥ በማጠብ ወይም ሰውነታችንን በመታጠብ ለውሃ መበከል አስተዋጽዖ እናደርጋለን፡፡ ይህንን ውሃ ምግባችንን ለማዘጋጀት ከተጠቀምን ምግባችን በጀርም እንዲበከል ስለምናደርግ በጤንነታችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት እናደርሳለን፡፡ ፋብሪካዎች ሲቋቋሙ ከውስጣቸው የሚወጣው መርዛማ ዝቃጭ ወንዞችን እንደሚበክል ካለማጤን የተነሳ ለፋብሪካ የሚያስፈልገውን የውሃ ፍጆታ ለማግኘት ሲባል ብቻ ፋብሪካዎች ወንዝ አቅራቢያ እንዲተከሉ ይደረጋል፡፡ ለዚህም አቃቂ ወንዝ አጠገብ የተቋቋመው የአቃቂ ጨርቃ ጨርቃ ፋብሪካና አዋሽ ወንዝ አቅራቢያ የተቋቋመው የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

በሀገራችን ንፁህ የመጠጥ ውሃ የሚያገኘው የሕዝብ ብዛት የተወሰነ ነው፡፡ በተቃራኒው የወራጅ ውሃ የሚጠቀመው ህዝብ ቁጥር ደግሞ በርካታ ነው፡፡ በመሆኑም ውሃንና የውሃ መቅጃዎችን በንጽህና ባለመጠበቅ የምንጠጣው ውሃ በቀላሉ ሊበከል ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል፤ ምክንያቱም እነዚህና መሰል ችግሮች ናቸው ዘላቂ ለሆነ የአየር ንብረት ለውጥ የሚዳርጉን፡፡

**(ምንጭ ከቀድሞ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የተወሰደ)**

**ድህረ ማዳመጥ**

**መምህር!**

በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በጽሑፍ በማሰራት የተማሪዎቹን የአዳምጦ መረዳት ደረጃ ይፈትሹ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ❖ ተማሪዎች ሶስት ሶስት ሆነው ለመወያየት እንዲዘጋጁ ይዘዟቸው፡፡
- ❖ ከዚያ በቀረቡላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
- ✓ ቡድን ሲመሰርቱ ፆታዊ ስብጥር ሊኖረው ይገባል፡፡
- ❖ በውይይቱ ሁሉም ተማሪዎች መሳተፍ እንደሚኖርባቸው መመሪያ ይስጧቸው፡፡
- ❖ በመቀጠልም ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ በተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- ❖ በሚወያዩበት ወቅት እየተዘዋወሩ የመከታተል ስራ ይስሩ፡፡
- ✓ ግር ያላቸው ጥያቄ ካለም ያብራሩላቸው፡፡
- ❖ በተጨማሪም የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብን ያስረዷቸው፡፡

- ❖ ባገኙት መርጃ መሳሪያ የተቀረፀ ክርክር እንዲመለከቱ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ከዚያ አራት አባላት ያለው ቡድን መስርተው በቀረቡላቸው የመከራከሪያ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲከራከሩ ያድርጉ፡፡

✓ በቡድኑ ውስጥ ፆታዊ ስብጥር ሊኖር ይገባል፡፡

- ❖ አከራካሪ ዳኛ አስመርጠው ማከራከር ይኖርብዎታል፡፡
- ❖ በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፤
- ❖ በማስጨብጨብ ወይም በሌላ ነገር ሊሆን ይችላል ማበረታቻ ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ❖ ሶስት ሶስት ሆነው ለመወያየት መዘጋጀታቸውን መፈተሽ፤
- ❖ ቡድኑ ፆታዊ ስብጥር ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ❖ ሁሉም ተማሪዎች ሀሳባቸውን በመግለፅ መሳተፋቸውን መገምገም፤
- ❖ በውይይቱ የመናገር ክሂላቸውን መፈተሽ፤
- ❖ አራት አባላት ያለው ቡድን መመስረት መቻላቸውን ማረጋገጥ፤
- ❖ የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያን መሰረት አድርገው መከራከር መቻላቸውን መዳሰስ፤
- ❖ ዳኛ በመምረጥ መከራከር መቻላቸውን መገምገም፤

**መርጃ መሳሪያ፡-**

- ➢ መቅረፀ ድምፅ
- ➢ ኮምፒውተር /ፕላዝማ/

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

### የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ❖ ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት መማሪያ መጽሐፉ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በማቅረብ በውይይት እንዲሳተፉና እንዲነቃቁ ያድርጉ፡፡
- ❖ ለቀረበላቸው ስዕል ጥልቅ ትንታኔ እንዲሰጡ ያለማምዷቸው፡፡
- ❖ ለማንበብ ፈቃደኛ ያልሆኑ ተማሪዎችን በማበረታታት ለቀጣይ ምንባብ እንዲዘጋጁ ያድርጉ፡፡
- ❖ በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያግባቧቸው፡፡

✓ የቀረበውን ስዕልም በፈቃደኝነት ገለፃ እንዲያደርጉላቸው ያበረታቷቸው፡፡

- ❖ በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡

**ጊዜ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- ❖ ተማሪዎቹ ምንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡
- ❖ ከዚያ ፈቃደኛ የሆነ ተማሪ በማስነሳት ድምፁን ከፍ አድርጎ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያነብላቸው ያድርጉ፡፡

✓ መስማት መቻል አለመቻላቸውን በመጠየቅ፣ መስማት እስኪችሉድረስ መጥነው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡

- ❖ ንብቡን ገታ አድርገው የማዳመጥ ሂደት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ "ለህይወት ማዘመን" እና "ይኸው እንደ ዋዛ" በሚል ርዕስ በቀረቡት ግጥሞች ውስጥ ያሉትን ቃላት ሀሳብ መመርመር እንዲችሉ ያግዟቸው፡፡
- ❖ መረዳት እስኪችሉ ድረስም ደጋግመው እንዲያነቡት መመሪያ ይስጧቸው፡፡

**ድህረ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

- ❖ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ ምክንያታዊ ሆነው መልሳቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ የስራቸውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዲችሉ እርማት ይስጧቸው፡፡
- ❖ በመቀጠልም በቃላቸው ሸምድደው ለጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፤
- ❖ "ለህይወት ማዘመን" የሚለውን ግጥም ሀሳብ ተረድተው በዝርው ጽሑፍ መልክ በአንድ አንቀፅ እዲፅፉት ይዘዟቸው፤

✓ የፃፉትን አንቀፅ ያርሙላቸው፤

✓ ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ❖ አንብበው መገንዘብ መቻላቸውን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በማሰራት መፈተሽ፤

- ለቀረበላቸው ስዕል ጥልቅ ትንታኔ መስጠት መቻላቸውን መቃኜት፤
- የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እየተከታተሉ መሆናቸውን መዳሰስ፤
- ካነበቡት ፅሁፍ ምን እንደተገነዘቡ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በማሰራት መገምገም፤
- የግጥሞችን ሀሳብ መረዳት መቻላቸውን መፈተሸ፤
- በዝርው መልክ የፃፉት አንቀፅ ሀሳብ ከግጥሙ ሀሳብ ጋር የሀሳብ አንድነት ያለው መሆን አለመሆኑን መገምገም፡፡

**መርጃ መሳሪያ፡-**

- የግጥም መጽሐፍ
- ወደዝርው ጽሑፍ የተቀየረ ግጥም

**መልመጃ አንድ፡-**

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡

፩. ሀሰት

፪. እውነት

፫. ሀሰት

፬. እውነት

፭. ሀሰት

፮. እውነት

፯. ሀሰት

**መልመጃ ሁለት፡-**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።**

፩. ሀ

፪. መ

፫. ለ

፬. መ

፭. ሐ

፮. ለ

፯. ሀ

፰. ሐ

፱. ሀ

**መልመጃ ሶስት**

**ከዚህ በታች የቀረበላችሁን ግጥም በጥሞና አንብቡና ለጥያቄዎቹ ከቀደመ እውቀታችሁ በመነሳት ምላሽ ስጡ።**

፩. ለ

፪. መ

፫. ሐ

፬. ሀ

፭. ለ

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- ❖ በመጀመሪያ ክፍል ሶስት "ንባብ" ላይ የቀረበውን ስዕል ክፍል አራት "ፅህፈት" ላይ ከቀረበው ስዕል ጋር በማነፃፀር ጥልቅ የሆነ ትንታኔ በፅሁፍ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በመቀጠልም የፃፉትን ፅሁፍ እርስ በዕርስ ተቀያይረው እንዲተራረሙ ይዘዟቸው፡፡
- ❖ ከዚያ የተማሪዎችን ደብተር በመሰብሰብ የጠሰጣጡትን እርማት ትክክለኛነት ይመልከቱ፡፡
  - ✓ ሲተራረሙ ስህተት ሰርተው ከሆን እርማት ይስጧቸው፧
- ❖ በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፧
- ❖ በቃልም ሆነ በሌላ ነገር ማበረታቻ ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ስዕሎችን በማነፃፀር በፅሁፍ ጥልቅ ትንታኔ መስጠት መቻላቸውን መፈተሽ፧
- የሰጡት ትንታኔ በስዕሉ ሊተላለፍ ከተፈለገው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን መቃኜት፧
- የፃፉትን ጽሑፍ እርስ በዕርስ ተቀያይረው መተራረም መቻላቸውን ማረጋገጥ፧
- የተሰጣጡትን እርማት ትክክለኛነት መገምገም፧

# ክፍል አምስት፡- ቃላት

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

- በቅድሚያ ተማሪዎች ምዕራፍ አንድ ላይ የተማሩትን የአውዳዊ ፍች ምንነት እንዲያስታውሱ ያድርጓቸው፡፡
    - ✓ ምሳሌ ተጠቅመውም መጠነኛ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- በመቀጠልም የዓረፍተነገሩን ፅንሰ ሀሳብ እንዲረዱ ይዘዟቸው፡፡
- አውድን መሰረት አድርገው፣ የቀረቡላቸውን ቃላት፣ በዓነገሮቹ ክፍት ቦታ በማስገባት፣ አሟልተው እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡
- አያይዘውም የቀረቡላቸውን ያልተለመዱ ቃላት ከፍችዎቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ይዘዟቸው፡፡
- በመጨረሻም ግብረመልስም ይስጧቸው፡፡
- እርማትም ያድርጉላቸው፡፡
- በቃላት አማካኝነት (ጥሩ፣ ጎበዝ፣ በጣም ጎበዝ) ወዘተ በማለት ማበረታቻ ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- የቃላት አውዳዊ ፍች ምንነትን ማስታወስ መቻላቸውን መገምገም፤
- የቀረቡላቸውን ዓረፍተ ነገሮች ፅንሰ ሀሳብ መረዳታቸውን መፈተሽ፤
- የቀረቡላቸውን ቃላት በዓረፍነነገሮች ክፍት ቦታ ላይ ማስፈር መቻላቸውን መዳሰስ፤
- ያልተለመዱ ቃላትን ከፍችዎቻቸው ጋር በትክክል ማዛመድ መቻላቸውን

**መመርመር ፧**

**መልመጃ አንድ**

ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ከቀረቡት ቃላት መካከል አውድን መሰረት አድርጋችሁ በመምረጥና ባዶ ቦታው ውስጥ በማስገባት ዓረፍተነገሩን አሟልታችሁ ፃፉ።

፩. ሀገረ ሰብዓዊ

፪. ወላፈን

፫. ዳጎስ

፬. መሻሻል

፭. ሳንካ

፮. ቤተ ምርምር

፯. አዘቦት

፰. ማዕረግ

**መልመጃ ሶስት**

**በ"ሀ" ስር የቀረቡትን ያልተለመዱ ቃላት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ፍቾቻቸው ጋር አዛምዱ።**

፩. ሠ

፪. ረ

፫. ቀ

፬. ሸ

፭. በ

፮. ሰ

፯. ሐ

፰. መ

# ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

## የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

**መምህር!**

- ✓ በመጀመሪያ የነጠላ ዓረፍተ ነገርንና የውስብስብ ዓረፍተ ነገርን ምንነት በተመለከተ ምዕራፍ ስምንት ላይ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያግዟቸው፡፡
- ✓ በምሳሌ አስደግፈውም መጠነኛ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- ✓ የቀረቡላቸውን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር እያሉ እንዲለዩ ያድርጓቸው፤
- ✓ ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ብለው ለመለየት የተጠቀሙበትን መስፈርት በግልፅ እንዲረዱ ያግዟቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ግብረመልስም ይስጧቸው፡፡
- ✓ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ✓ በቃላት አማካኝነት ወይም በሌላ በሚችሉት ነገር ማበረታቻ ያድርጉላቸው፡፡

ምዘና

- የውስብስብና የነጠላ ዓረፍተነገርን ምንነት በተመለከተ ማስታወስ መቻላቸውን መፈተሽ፤

የቀረቡላቸውን ዓረፍተነገሮች ነጠላና ውስብስብ እያሉ መለየት መቻላቸውን መገምገም፤

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ ወይም ውስብስብ ዓርፍተ ነገር በማለት መልሱ።**

፩. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

፪. ነጠላ ዓረፍተ ነገር

፫. ነጠላ ዓረፍተ ነገር

፬. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

፭. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

፮. ነጠላ ዓረፍተ ነገር

፯. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

፰. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

፱. ነጠላ ዓረፍተ ነገር

# ምዕራፍ አስር

# ተውኔት

(12 ክፍለ ጊዜ)

**የምዕራፉ አላማዎች፣ ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-**

- ስለ ተውኔት ምንነት ትንታኔ ይሰጣሉ፤
- የጽሑፉን ሀሳብ አዳምጠው ይተነትናሉ፤
- የተውኔት አላባውያንን ይዘረዝራሉ፤
- በጽሑፍ ውስጥ የተለያዩ አያያዦችን ይጠቀማሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች**

- አዳምጦ መተንተን
- ጽሑፍን መተረክ
- የሚና ጨዋታ
- የድራማ ጽሑፍ
- ዘይቤ
- መስተጻምር

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ለሁሉም ጊዜ አለው!

## የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር**! "ለሁሉም ጊዜ አለው!" የሚለውን ተውኔት ተማሪዎችዎን በትዕዛዝ ከማሰራትዎ በፊት፡-

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- የሚያነቡላቸውን ተውኔት አዳምጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ያድርጉ፡፡
- በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያግባቧቸው፡፡
- ✓ አያይዘውም ስዕሉን በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ተቀምጠው እንዲከታተሉ ያድርጓቸው፡፡

**ጊዜ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- በመቀጠልም ምንባቡን በዝግታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- መስማት መቻል አለመቻላቸውን በመጠየቅ ድምፅዎን ከፍ አድርገው ያንብቡላቸው፡፡

- ተማሪዎችዎ ለሚሰጧቸው ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠልም ተወኔት በትዕዛዝ እንዴት እንደሚሰራ ያስረዷቸው፡፡
- ✓ ለአይነስውራን ተማሪዎች በቂ ማብራሪያ ይስጧቸው፤ ጓደኞቻቸውም እንዲያግዟቸው ያግባቧቸው፡፡
- ትንሽ ቅንጫቢ (የተቀረፀ ተውኔት) አምጥተው ባገኙት ኮምፒውተር እንዲመለከቱ ያግዟቸው፡፡

**ድህረ ማዳመጥ**

**ትዕዛዝ**

- የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በቃልና በጽሑፍ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡
- በመጨረሻም ተውኔቱን በትዕዛዝ ያሰሯቸው፡፡
- ✓ በሰሩት ተውኔት ላይ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በሚችሉት አቅም ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- ተውኔትን በተመለከተ ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- የቀረበላቸውን ተውኔት በትኩረት መከታተላቸውን መቃኘት፤
- የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን መስራት መቻላቸውን መዳሰስ፤
- ተውኔቱን በትዕዛዝ መስራት መቻላቸውን መገምገም፤

መርጃ መሳሪያ፡-

- ኮምፒውተር /ፕላዝማ/
- ራዲዮ
- መቅረፀ ድምፅ

## ለሁሉም ጊዜ አለው!

በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ዛፍ፣ የተለያዩ መቀመጫዎች፣ እልፍ ሲሉ ደግሞ የመማሪያ ክፍሎች ይታያሉ፡፡ ጊዜው የእረፍት ሰዓት ነው፡፡ አበበችና መዓዛ የእረፍት ሰዓታቸውን ተጠቅመው እጅ ለእጅ በመያያዝ እየተጫወቱ በግቢው አበቦች መካከል ይዘዋወራሉ፡፡ ሁለቱም የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ክልላዊ ፈተና ሊፈተኑ ደግሞ ሶስት ወር ያህል ቀርቷቸዋል፡፡

መዓዛ፡- ማስተዋል የጎደላቸው ሰዎች የሰውን ሕይወት ከመጉዳት አይመለሱም፡፡

(አለች የአበበችን እጅ ጨበጥ አድርጋ)

አበበች፡- ደግሞ ዛሬ ምን አጋጠመሽ? ክፍል ውስጥም ሳይሽ ትምህርሽን እንደ

ወትሮሽ በንቃት ስትከታተይ አልነበረም፡፡

መዓዛ፡- ደብዳቤ ጻፈልኝ እኮ!

አበበች፡- ማን? ማቲያስ!

መዓዛ፡- አዎ!

አበበች፡- ምን ብሎ?

መዓዛ፡- ይገርምሻል! እኔ በሰፈር ልጅነቱ እንደጓደኛዬ ነው የማየው፡፡ የትምህርት

መሳሪያዎችም እንዋዋሳለን፡፡ አንዳንዴም በአንዳንድ ትምህርታዊ ጥያቄዎች ላይ ላይ ላይ ላይ እንወያያለን፡፡ ይህንን ድንበር ጥሶ ዛሬ የፍቅር ደብዳቤ ጻፈልኝ፡፡ አይገርምሽም?

አበባች፡- ታዲያ ምናለበት? (አለች አበበች ትንሽ ሳቅ ብላ)

መዓዛ ፡- ምናለበት! (እንደብራቅ ጮኻ እጇን መንጭቃ ከአበበች አላቀቀችና)

በአሁኑ ሰዓት የኔ ዓላማ የፍቅር ጥያቄን ማስተናገድ ሳይሆን ትምህርቴን አጥንቼ ፈተናዬን ማለፍ ነው፡፡ ገባሽ (ብላ አፈጠጠችባት)፡፡

አበበች፡- ምን አስቆጣሽ? እኔ እኮ የቀልዴን ነው፡፡ (አለች አበበች ፊቷ ላይ

ድንጋጤ እየተነበበባት)

መምህር!

ተማሪዎች ለማዳመጥ ክሂል የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ እየተከታተሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሾቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

- አበበችንና መዓዛን ያጋጯቸው ነገር ምንድን ነው?
- ማቲያስ የሰራው ስራ ተገቢ ነው ትላላችሁ? እንዴት?
- አበበችና መዓዛ እርቅ የሚያወርዱ ይመስላችኋል?

**መዓዛ፡-** ለዚህ አይነት ቀልድ ቦታ አልሰጠውም፡፡ አንቺም ብትሆኚ ከትምህርት ውጪ ሌላ ስሜትና ፍላጎት ካለሽ አልፈልግሽም፡፡ ለማግባባት የምታደርጊው ሙከራ መሆኑንም አውቄብሻለሁ፡፡ እንዲያውም ትላንት ያለወትሯችሁ ከማትያስ ጋር አፍ ለአፍ ገጥማችሁ ስታወሩ በርቀት አይቻችኋለሁ፡፡ ይህ መሆኑ ግን አልገባኝም ነበር፡፡ ያሳዝናል በጣም! (አለች በቁጭት)፡፡

**አበበች፡-** (ትንሽ አሰብ አደረገችና) እሺ ይቅርታ አድርጊልኝ፡፡ ስሜትሽን

እንደጎዳሁት የገባኝ አሁን ነው፡፡ ለደብዳቤው ግን መልስ መስጠት አለብሽ (አለቻት በለሰለሰ አንደበት)

**መዓዛ፡-** ደብዳቤ የምጽፍበትን ጊዜ የቤት ስራዬን እሰራበታለሁ፡፡ ዓላማህን

የማታውቅ ጉዞህን የዘነጋህ ተማሪ ነህ ብለሽ ንገሪው፡፡ ይኸው ይበቃዋል፡፡

**አበበች፡-** መአዚ ግን የፍቅር ጓደኛ ቢኖርሽ ምን ችግር አለው? ሰው ባንድ ጊዜ

ሁለት ነገር ማድረግ አይችልም ማለት ነው? “ለሰው መድሃኒቱ ሰው ነው” ይባል የለ?

**መዓዛ፡-** አጥፊውም እኮ ሰው ነው፡፡ በዚያ ላይ “ለሁሉም ጊዜ አለው” ሲባል

አልሰማሽም፡፡ አሁን የኛ ጊዜ የምንማርበት ትልቅ ደረጃ ለመድረስ መሰረት የምንጥልበት እንጂ እንደዚህ አይነት ሕይወት ውስጥ የምንገባበት ዕድሜ ላይ አይደለንም፡፡ ዛሬ የሚያብለጨልጥ፣የሚያምር ነገር ሁሉ ነገን ከቻልን የኛ ናቸው፡፡ ነገን ለመኖር ደግሞ የዛሬ አረማመዳችንን ማስተካከል ይኖርብናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከአሁን በኋላ ውይይት የለም፡፡ አንቺም ብትሆኚ እንዳታነሺብኝ፡፡ (አለች መዓዛ ኮስተር ብላ፡፡ ወዲያው ተደወለና ወደ ክፍል ገቡ፡፡

**(ከቀድሞው የስምንተኛ ክፍል መፅሃፍ ተሻሽሎ የተወሰደ)**

## አዳምጦ መረዳት

> **መምህር!**
>
> በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በጽሑፍ በማሰራት የተማሪዎቹን የአዳምጦ መረዳት ደረጃ ይፈትሹ፡፡

### መልመጃ ሁለት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡**

፩. ሐ

፪. ለ

፫. መ

፬. ሀ

፭. መ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

**መምህር!**

- በመጀመሪያ ተማሪዎች በቀረቡላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ቡድን መስርተው እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡
- የሚመሰርቱት ቡድን የፆታ ስብጥር እንዲኖረው ይዘዟቸው፡፡
- በውይይቱ ሁሉም ተማሪዎች መሳተፍ እንደሚኖርባቸው መመሪያ ይስጧቸው፡፡
- በመቀጠልም ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ በተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- በተጨማሪም ጥንድ ጥንድ በመሆን የጋዜጠኛንና የእንግዳን ገፀባህርይ ተዋርሰው የቀረበላቸውን የሚና ጨዋታ በትዕዛዝ እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ሚናቸውን በሚገባ እንዲወጡ ያግዟቸው፡፡
- በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፤
- በማስጨብጨብ ወይም በሌላ የማነቃቂያ ቃል ማበረታቻ ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ቡድን መስርተው ለመወያየት መዘጋጀታቸውን መፈተሽ፤
- ሁሉም ተማሪዎች ሀሳባቸውን በመግለፅ መሳተፋቸውን መገምገም፤
- በውይይቱ የመናገር ክሂላቸውን መፈተሽ፤
- ጥንድ ጥንድ ሆነው የጋዜጠኛንና የእንግዳን ሚና በትዕዛዝ ለማሳየት መዘጋጀታቸውን መፈተሽ፤

- ❖ የተሰጣቸውን ሚና መወጣት መቻላቸውን መገምገም፤

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

### የትምህርቱ አቀራረብ

**ቅድመ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

**መምህር!**

ተውኔቱን በትዕዛዝ ከማሰራትዎ በፊት፡-

- ❖ መማሪያ መጽሐፉ ላይ ያሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በማቅረብ በውይይት እንዲሳተፉና እንዲነቃቁ ያድርጉ፡፡
- ❖ በክፍልዎ ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያግባቧቸው፡፡
  - ✓ የቀረበውን ስዕልም በመግለፅ እንዲያግዟቸው ያድርጉ፡፡
- ❖ በተጨማሪም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ከፊት ወንበር ያስቀምጧቸው፡፡
- ❖ አያይዘውም የተውኔትን ምንነት በተመለከተ ማስታወሻ እንዲይዙ ያድርጓቸው፡፡
- ❖ በመቀጠልም ተውኔቱን ስምንት ስምንት ሆነው ቡድን በመመስረት መለማመድ እንዲችሉ ያግዟቸው፡፡
- ❖ በሚመሰረተው ቡድን ውስጥ ቢያንስ አንድ ሴት መኖር እንደሚኖርበት ያስረዷቸው፡፡
  - ✓ ሴቶች የወንዶችን ገፀባህርይ መስለው መጫወት እንደሚችሉም ያስገንዝቧቸው፡፡
- ❖ ጊዜ ወስደው በሚገባ መለማመድ እንደሚኖርባቸው መመሪያ

ይስጧቸው፡፡

**ጊዜ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

❖ ተማሪዎቹ ተውኔቱን በለሆሳስ እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡

✓ ተውኔቱ ላይ ምልልስ በማድረግ የተሳተፉትን ገፀባህርያት ቁጥር የሚያሟሉ ተማሪዎችን በመመልመል ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በምልልስ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

❖ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች መስማት መቻል አለመቻላቸውን በመጠየቅ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያቀርቡላቸው ያድርጉ፡፡

❖ በተጨማሪም የአቅራቢዎችን የከንፈር እንቅስቃሴ በመከታተል እንዲረዱ ምክር ይስጧቸው፡፡

❖ ተውኔቱ እየቀረበ እያለ በመሀል ጥያቄዎችን በመጠየቅ በንቃት እንዲከታተሉ ያድርጉ፡፡

**ድህረ ንባብ**

**ትዕዛዝ**

❖ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲሰሩ በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ ምክንያታዊ ሆነው መልሳቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤

❖ ለሰሩት ስራም እርማት ይስጧቸው፡፡

❖ በመጨረሻም ተውኔቱን በቃላቸው ሸምድደው ለጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፤

✓ አቅርቦታቸውን ተመልክተው ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

✓ በቃልም ሆነ በሌላ በሚችሉት ነገር ያበረታቷቸው፡፡

**ምዘና**

- ❖ አንብበው መገንዘብ መቻላቸውን መፈተሽ፤
- ❖ ከተውኔቱ ምን እንደተገነዘቡ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በማሰራት መገምገም፤
- ❖ ስለተውኔት አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን መዳሰስ፤
- ❖ ቢያንስ አንድ ሴት ያለበት ባለ ስምንት አባላት ያለው ቡድን መመስረታቸውን ማረጋገጥ፤
- ❖ ተውኔቱን በትዕዛዝ መስራት መቻላቸውን መገምገም፤

## የተውኔት አይነቶች

- ❖ አራት ዋና ዋና የተውኔት አይነቶች አሉ፡- እነሱም፡-

**፩. ትራጀዲያዊ ተውኔት**፡- የገሀዱ ዓለም ሰዎች ሊገጥሟቸው የሚችሉ አሳሳቢ ችግሮች ላይ የሚያተኩር የተውኔት አይነት ነው፡፡ በጥቅሉ ትራጀዲ ሁለት የተውኔት ድባቦች ይኖሩታል፡፡ እነዚህም ጭፍን ድባብና ብርሃናማ ድባብ ናቸው፡፡

- ➢ ጭፍን ድባብ ፍርሃትን፡- ሰቀቀንን፣ ራሮትን፣ ቀቢጸ ተስፋንና ግብዓተ መሬትን የሚያሳስብ ሲሆን፤
- ➢ ብርሃናማ ድባብ ደግሞ እርቅን፣ ሰላምን፣ ሚዛናዊ ብይንን፣ ደስታንና ተስፋን ያሰርጻል፡፡ በስነ ልቦና ደረጃም ድህነትንና ትንሳኤን የሚያጭር ነው፡፡

በዘይቤአዊ አነጋገር አንደኛው የምንወረወርበትን የእሳት ጉድጓድ እያሳየን የሚያስበረግገን አይነት ስሜት ሲጭርብን፣ ጽንፈኛ ተቃራኒው ደግሞ ሕይወት ወደ ሰገነት የምታቀናበትን ጉዞ ያመላክተናል፡፡ ባጭሩ ትራጀዲ ያስጨንቃል፣

ፀጉር ያቆማል፣ ያኮሳትራል፣ ይጎመዝዛል፡፡

**፪. ኮሜዲያዊ ተውኔት፡-** አንዳንድ ሰዎች ኮሜዲን እንደ አስቂኝ ተውኔት አድርገው ለማጠቃለል ይሞክሩ ይሆናል፡፡ ኮሜዲን አስቂኝ ተውኔት ነው ብሎ መደምደም ቁምነገረኛ ባህርይውን ለመዘንጋት ያጋልጣል፡፡ ኮሜዲ እያዝናና ለማስተማር የሚያገለግል ተውኔት አይነት ነው፡፡ ኮሜዲ በርካታ መልኮች ቢኖሩትም፣ በጥቅል ሲታይ ግን የቁም ነገር ተውኔት ነው፡፡ የሚያነጣጥረው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በሚታዩ ማህበራዊ ድክመቶች ላይ ነው፡፡ ድክመቶችን በገጸባህሪያት አኗኗር ላይ በማውጣትና በማሳየት አቃቂራዊ በሆነ መልክ ወደ መድረክ ያቀርባቸዋል፡፡

ስለ ኮሜዲ ለመነጋገር ዋናው ጉዳይ ድባቡ መሆን አለበት፡፡ የኮሜዲ ድባብ የተረጋጋ፣ ብርሃናማና ተስፋ የሚሰጥ ነው፡፡ ኮሜዲ ከዘመን ዘመን ወይም ከአንዱ ማህበራዊ አውድ ወደ ሌላው ለመሸጋገር ያለው አቅም ዝቅ ያለ ነው፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የሚሆነው በወቅቱ በሚታዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ማፍጠጥ ስለሚቀናው ነው፡፡ እነዚህም የወቅቱ ዐውዳዊ የሆኑ ሰብአዊ ገጠመኞች ውለው አድረው ይሻሻላሉ፤ ይሻራሉም፡፡ ከዚያም በሌላ ማህበራዊና ባህላዊ ስርዓቶችና ወጎች ይተካሉ፡፡

**፫. ቧልታይ ተውኔት**፡- ጥሬ ፍችው የረባውንም ያልረባውንም ፍሬ ቢስ ወሬ ማነብነብ ማለት ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን ይህ ጽንሰ ሀሳብ ትክክል አለመሆኑ መታየት ጀመረና የቧልታይ ተውኔት አዝናኝነት ዋጋ እያገኘ መጣ፡፡ የዚህ ተውኔት ዋነኛ ግብ፣ በዚህም- በዚያም ብሎ፣ ሳቅ ማጫር ነው፡፡ የማይመስሉ አንዳንዴም ሊሆኑ የማይችሉና ተግባሮቻቸውን ጅላጅል የሚያደርጉ ሁኔታዎች ወደ መድረክ በማምጣት በታዳሚው ውስጥ ሳቅ እንዲቀሰቅስ ይደረጋል፡፡ ገጸ ባህሪያቱ የሚከሰቱበት ጉዳይ ሳይኖር ድንገት ከተፍ ይላሉ፡፡ ልክ እንደ እርጎ

ዝንቦች! በማያገባቸው ነገርም ዘው ብለው ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ከዚህም በላይ የማይችሉትን ነገር ለማድረግ በመቃጣትና ውድቀትን በማትረፍ በከላባነታቸውም፣ በጅልነታቸውም፣ እንድንስቅባቸው ያደርጋሉ፡፡

የቧልታይ ተውኔት ለተውኔት አለባውያን ይገዛ አይባልም፡፡ ለምሳሌ አንዳንዴ ቃለ ተውኔትም ላያስፈልገው ይችላል፡፡ ገጸባህርይው በጅላጅልነት ችሎታው፣ በአካል ቅልጥፍናው ወይም በእንቅስቃሴው ብቻ በሳቅ ጎርፍ ሊያጥለቀልቀን ይችላል፤ ወይም በትውናው ወቅት በሚያጋጥሙ ሁኔታዎች መነሻነት ደራሲው ያላዘጋጃቸውን ሊያስቁ የሚችሉ ቃላት ሊናገር ይችላል፡፡

**ድንቃይ ተውኔት፡-** ዋነኛ ባህርይው ቅይጥነቱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከቀሪዎቹ የተውኔት አይነቶች የሚዋሳቸው የስሜት (የድባብ)፣ የድርጊያና የውጤት መልኮች ይታዩበታል፡፡

ድንቃይ ተውኔት አላማው ተደራሲውን በድንገት በተቀሰቀሰ ስሜት አስጋልቦ ከድል ቦታ ማድረስ ስለሆነ፣ ስለገጸባህሪያቱ ሕሊናዊ አሳሳል መጨነቅ የተውኔቱ ስራ አይደለም፡፡ ተደራሲው ቶሎ ብሎ መልካሞቹን ለማወደስና እኩያኑን ለመራገም በተጻራሪ (በፍቅርና በጥላቻ) ረድፍ እንዲሰለፉ ለማድረግ እንዲችል የሚያደርግ ነው፡፡ ስለዚህም ተደራሲው የሚወዳቸው ገጸ ባህሪያት አሽቃባጮች፣ እንስፍስፎች  ወይም ምሳር በአንገቴዎች ሆነው ይሳላሉ፡፡

ድንቃይ ለአላባውያን አይገዛም፡፡ ይህም ከቧልታይ ጋር ያመሳስለዋል፡፡ የተዋጣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የተዋጣ ሴራና የበሰለ የገጸ ባሕሪያት አቀራረፅ ከድንቃይ እጅ አይጠበቁም፡፡ በድርጊት የተሞላ መሆኑ፣ ከጸሃፌ ተውኔቱ ችሎታ ይልቅ የተዋንያኑን ብቃት መጠየቁ፣ ለፊልም ጥበብነት መቅረቡ፣ ወዘተ ከቧልታይ ተውኔት ጋር የሚያመሳስሉት ጠባያቱ ናቸው፡፡

**መልመጃ አንድ፡**

በተውኔቱ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።

፩. እውነት

፪. ሀሰት

፫. እውነት

፬. ሀሰት

፭. ሀሰት

**መልመጃ ሁለት**

**በተውኔቱ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።**

፩. ሀ

፪. ለ

፫. ሐ

፬. መ

፭. ሀ

**መልመጃ ሶስት**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

፩. ለ

፪. መ

፫. ሐ

፬. መ

፭. ሀ

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

## የትምህርቱ አቀራረብ

## ትዕዛዝ

**መምህር!**

- በመጀመሪያ ጠልፎ በኪሴ በሚል ርዕስ የቀረበውን ተውኔት በትዕዛዝ ከመስራታቸው በተጨማሪ ሀሳቡን መረዳት እስኪችሉ ድረስ ደጋግመው ማንበብ እንደሚኖርባቸው ይዘዟቸው፡፡
- በመቀጠልም የተውኔቱን ሀሳብ ተረድተው በራሳቸው አገላለፅ በሁለት አንቀፅ እንዲፅፉት ያድርጓቸው፡፡
- የፃፉትን አንቀፅ እርስ በዕርስ በመቀያየር ሂስ እንዲደራረጉ እና እንዲተራረሙ ይዘዟቸው፡፡
- የጻፉትን አንቀፅ ሀሳብ ከተውኔቱ ሀሳብ ጋር በማነፃፀር ያርሙላቸው፡፡
- በተጨማሪም አንድ የተውኔት ርዕስ መርጠው አጭር ተውኔት እንዲፅፉ ይዘዟቸው፡፡
    - ✓ በሚፅፉበት ወቅት የተውኔትን መሰረታዊ ባህርያትና የተውኔትን ሙያዊ ቃላት ታሳቢ እንዲያደርጉ ይንገሯቸው፡፡
- በመጨረሻም ግብረመልስ ይስጧቸው፤
- በቃላት አማካኝነትም ማበረታቻ ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ተውኔቱን መረዳት እስኪችሉ ድረስ ደጋግመው ማንበባቸውን መከታተል፤
- የተውኔቱን ሀሳብ ተረድተው በራሳቸው አገላለፅ በሁለት አንቀፅ መፃፍ መቻላቸውን መፈተሽ፤
- የፃፉትን አንቀፅ ተቀያይረው ሂስ መደራረጋቸውንና መተራረማቸውን መገምገም፤
- ርዕስ መርጠው በራሳቸው አጭር ተውኔት መፃፋቸውን ማረጋገጥ፤
    - ✓ የፃፉት ተውኔት የተውኔትን ባህርያትና ሙያዊ ቃላት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን መፈተሽ፤

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ትዕዛዝ

**መምህር!**

- በቅድሚያ ተማሪዎች የዘይቤን ምንነት በተመለከተ አጭር ኖት እንዲይዙ ያድርጓቸው፡፡
- በመቀጠልም ዋና ዋና የሚባሉትንና ለደረጃቸው ይመጥናሉ ተብለው የቀረቡትን የዘይቤ አይነቶች በምሳሌ አስደግፈው በማስረዳት እንዲገነዘቧቸው ለማድረግ የሚችሉትን ያድርጉ፡፡
- አያይዘውም በቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉትን የዘይቤ አይነቶች መለየት እንዲችሉ እገዛ ያድርጉላቸው፣
- የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች በፅሁፍ ያሰሯቸው፡፡
- በመጨረሻም ግብረመልስም ይስጧቸው፤
- ማበረታቻም ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- ዘይቤን በተመለከተ ማስታዎሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤

- የዘይቤን ምንነት መረዳት መቻላቸውን መገምገም፤
- የዘይቤ አይነቶችን መለየት መቻላቸውን መፈተሽ፤

በቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉትን ዘይቤዎች መለየት መቻላቸውን መዳሰስ፤

## ዘይቤ

ለአገላለፃችን ጥንካሬ በመስጠት የምናስተላልፈው መልዕክት ጎልቶ ወይም ግልፅ ሁኖ እንዲታይ ለማድረግ የምንጠቀምበት አባባል ወይም የአነጋገር ስልት ነው።

## የዘይቤ አይነቶች

**አነፃፃሪ ዘይቤ**፡- ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን በማንሳት ከባህርይ፣ ከድርጊትና ከመሳሰሉት ነገሮች አንፃር እንደ፣ ይመስላል፣ ያክላል፣ ይፎካከራል ወዘተ የመሳሰሉ የማነፃፀሪያ ቃላትን በመጠቀም የማወዳደር ስራ ሚሰራበት የዘይቤ አይነት ነው።

ምሳሌ፡- የልጁ ጥቁረት ጥቅጥቅ ጨለማ ይመስላል።

፪. **ተለዋጭ ዘይቤ**፡- የአንዱን ባህርይ ለሌላው በመስጠት የሚፈጠር የዘይቤ አይነት ነው።

- በዚህ ዘይቤ ማነፃፀር አለ፤ የማነፃፀሪያ ቃላትን ግን አይጠቀምም።

ምሳሌ፡- ንግግሯ ሬት ነው።

፫. **ሰውኛ ዘይቤ**፡- የሰውን ልዩ ልዩ ባህርይ ለሌሎች ነገሮች ለዕንስሳት፣ ለተክሎችና ለግዑዛን ነገሮች በመስጠት የሚፈጠር የዘይቤ አይነት ነው።

ምሳሌ፡-ለሰው ሞት አነሰው አለች ቀበሮ።

፬. **እንቶኔ ዘይቤ**፡- በአጠገባችን <u>የሌለን</u> ሰው /ሰው ያልሆነ ነገር/ በቅርብ እንዳለና

መልስ እንደሚሰጠን በማሰብ የምንጠይቅበት፣ የምንማፀንበት፣ የምናማርርበት የዘይቤ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- እባክህን ቴዎድሮስ ቀና ብለህ ይህን ትውልድ ተመልከተው!

፫. **አያዎ ዘይቤ**፡- ሁለት ተቃራኒ ሀሳብ በሚይዙ ሀረጎች ወይም ዓ.ነገሮች የሚፈጠር የዘይቤ አይነት ነው፡፡

- ሀሳቦቹ ከላይ ሲያዩዋቸው ሀሰት የሚመስሉ ሲመረመሩ ግን እውነታን የያዙ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-ላለመማር መማር ወዘተ.

፬. **ምፀት ዘይቤ፡-** የማፌዝ፣ የማሽሟጠጥ ወይም የማላገጥ ስራ የሚሰራበት የዘይቤ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ፊቱን ኮስኩሶ የመጣን ተማሪ ---ዛሬ ፊትህ በደስታ ያበራል! ማለት

፭. **ግነት ዘይቤ፡-** ትንሽ እውነታን አጉልቶና አግዝፎ ለማቅረብ የሚያገለግል የዘይቤ አይነት ነው፡፡

- ምሳሌ፡- የሰማይ ስባሪ የሚያክል ዳቦ ሰጠኝ፡፡

**፮. ተምሳሌት ዘይቤ፡-** ይህ የዘይቤ ዓይነት አንድ ነገር ራሱን ላልሆነ ነገር በውክልና ሲቆም **የሚታበት** የዘይቤ ዓይነት ነው፡፡

ሶስት አይነት የተለመዱ የተምሳሌት ዘይቤ አይነቶች አሉ፡፡

- አንደኛው የተምሳሌት አይነት ሁለንተናዊ (ዓለምአቀፋዊ) የሚባለው ነው፡፡ አበባን ለፍቅርና ለውበት፣ ጨለማን ለድንቁርና ለመጥፎ አጋጣሚ፣ ወርቅን ለውድና ለክቡር ነገር፣ ውሃን ከክፉ ስራ ለመንጻት ለመታደስ፤ ተራራን

ለማይጋፋት ከፍተኛ ሀይል ተምሳሌት ማድረግ የተለመደ ነው፡፡

- ✓ እንዲሁም የጸሀይን መውጣት ለመታደስ፣ እንደገና ለመፈጠር፣ ለነጻነት፣ እሳትን ለጥፋት ለመከራ፣ ርግብን ለሰላም መወከል አለማቀፋዊ ልምድ መሆኑ ይነገራል፡፡

- ➢ ሁለተኛው የተምሳሌት አይነት ተለምዷዊ (ሀገርአቀፋዊ) የሚባለው ነው፡፡ ይህ በአንድ ማህበረሰብ ወግና ልማድ እንዲሁም የአኗኗር ስርዓትና ሕይወታዊ ገጠመኝ መሰረትነት የሚፈጠር ነው፡፡ በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገኙ ተምሳሌቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የኖሩ፣ ህዝቡ በቀላሉ የሚያውቃቸውና በልማዳዊ ስምምነት የተቀበላቸው ናቸው፡፡

  - ✓ ለምሳሌ፡- በኢትዮጵያ በአብዛኛው ክፍል ጥቁር ልብስ ሀዘንን፣ ነጭ ልብስ ደግሞ ደስታን ይወክላል፡፡ በህንዶች ደግሞ የሀዘንና የትካዜ ምልክት ሆኖ የሚያገለግለው ነጭ ልብስ እንደሆነ ይነገራል፡፡

- ➢ ሶስተኛው አይነት ተምሳሌት ግላዊ (ግለሰብዓዊ) የሚባለው ነው፡፡ ይህ በደራሲው ምልከታና ምናብ ለነገሮች የተለየ ፍች ለመስጠት የሚፈጠር ሲሆን የደራሲው አሻራ፣ ለህይወትና ለተፈጥሮ ያለው አተያይ የሚንጸባረቅበት ነው፡፡ ውክልናውን ተረድቶ የቅኔውን ምስጢር ለመፍታት ጥልቅ ምርመራን ይጠይቃል፡፡

**፱. ምስያ ዘይቤ፡-** ይህ ዘይቤ አንድን ሀሳብ፣ ድርጊት፣ ሁኔታ፣ ባህሪ ወይም ተፈጥሮ በባህሪም ሆነ በቅርጽ ተመሳሳይ ይሆናል ተብሎ የተገመተን ነገር አብሮ በማምጣት የፊተኛው የኋለኛውን ይበልጥ እንዲያጎላውና እንዲያደምቀው ለማድረግ የሚገባ ነው፡፡

**፲. ንቡር ጠቃሽ ዘይቤ፡-** ታሪክን፣ አፈታሪክን፣ ተረትን፣ ሀተታ ተፈጥሮን ታሪካዊ

በታዎችን፣ ዜና መዋዕልን፣ መጽሃፍ ቅዱስን፣ ቅዱስ ቁርአንን፣ ገድልን፣ ዜና መዋዕልን፣ ታላላቅ የኪነጥበብ ስራዎችን ወዘተ… በማስታወስና በመጥቀስ ላይ የሚመሰረት የዘይቤ ዓይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- እንደ ጎልያድ እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ!

**፲፩. በስመ ሀዳሪ ዘይቤ፡-** ይህ አይነቱ ዘይቤ አንድን ነገር በራሱ ሳይሆን በሚካለልበት ወገን የሚጠራ የዘይቤ አይነት ነው፡፡

ለምሳሌ፡- "አፍሪካ ከተረጂነት መላቀቅ አለባት!" የሚለው አገላለጽ አፍሪካን ጠርቶ ስለ ህዝቦቿ የሚናገር ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ደግሞ፣ "ከታላቁ ቅጥር ግቢ የቅኔ ወንበር ተዘርግቷል" የሚል አገላለጽ ብንሰማ የቅኔ መምህሩ ማስተማር መጀመራቸውን እንረዳለን፡፡

**መልመጃ አንድ**

**በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን የዘይቤ አይነቶች ፃፉ፡፡**

፩. ግነት ዘይቤ

፪. እንቶኔ ዘይቤ

፫. አያዎ ዘይቤ

፬. ሰውኛ ዘይቤ

፭. ተለዋጭ ዘይቤ

፮. ተነፃፃሪ ዘይቤ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

## የትምህርቱ አቀራረብ

## ትዕዛዝ

**መምህር!**

- ✓ በመጀመሪያ የመስተፃምርን (የአያያዥ ቃላትን) ምንነት በተመለከተ አጭር ማስታዎሻ እንዲይዙ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ በምሳሌ አስደግፈውም መጠነኛ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡

በመቀጠልም፡-

- ✓ በቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች ክፍት ቦታ ላይ በሰንጠረዥ ውስጥ ከቀረቡላቸው አያያዥ ቃላት እየመረጡ በማስገባት መሙላት እንዲችሉ ያግዟቸው፡፡
- ✓ አያይዘውም መስተፃምሮችን ተጠቅመው ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ትእዛዝ ይስጧቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡
- ✓ በቃላት አማካኝነት ማበረታቻ ያድርጉላቸው፡፡

**ምዘና**

- የመስተፃምርን (የአያያዥ ቃላትን) ምንነት በተመለከተ አጭር ማስታወሻ መያዛቸውን መፈተሽ፤
- በቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ትክክለኛ አያያዥ ቃል ማስገባት መቻላቸውን መገምገም፤
- አያያዦችን ተጠቅመው ዓረፍተነገር መመስረት መቻላቸውን መዳሰስ፤

**መልመጃ አንድ**

**ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ከቀረቡት አያያዥ ቃላት መካከል ተገቢ የሆኑትን በመምረጥ ከታች ያሉትን ዓረፍተነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

| | |
|---|---|
| ፩. ቢሆንም | ፭. ግን |
| ፪. እንዲሁ | ፮. አለበለዚያ |
| ፫. ስለሆነ | ፯. ወይም |
| ፬. ነገር ግን /ግን/ | ፰. ስለ |

## ዋቢ ጽሑፎች


ሕይወት እምሻው፡፡ 2010፡፡ *ፍቅፋቂ* ፡፡ አ.አ፣ፋር ኢስት አሳታሚ ድርጅት፡፡

መስፍን ሀ/ማርያም፡፡1976፡፡ *የቡና ቤት ሥዕሎችና ሌሎችም ወጎች፡፡* አ.አ፣ የኢትዮጵያ መጻህፍት ድርጅት፡፡

መንግስቱ ለማ ፡፡1953፡፡ *የተውኔት ጉባዔ፡፡* አ.አ፣ ተራመድ ማተሚያ ቤት፡፡

ምህረት ሞገስ ፡፡ አዲስ ዘመን፣ ጥር 25/ 2012፡፡

ምስራቅ ተረፈ፡፡ 2009፡፡ *ጨው በረንዳ፡፡* ፋር ኢስት ማተሚያ ድርጅት፡፡

በዕውቀቱ ስዩም ፡፡ 2001፡፡ *ስብስብ ግጥሞች፡፡* አ.አ፣ ፋርኢስት ትሬዲንግ፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡2009፡፡ *ያልተከፈለ ስለት፡፡* አ.አ፣ እሌኒ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ባየ ይማም፡፡ 2002፡፡ *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡* አ.አ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ሰለሞን ሀለፎም፡፡1997፡፡ *የድርሰት አጻጻፍ፡፡* አ.አ፤ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

ሲሣይ መንግስቴ፡፡2006፡፡ *ለባሕልና ቱሪዝም ኢንስቲቱት የፓናል ውይይት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣* ያልታተመ፡፡

ሳህሉ አክሊሉ እና ፋንቱ ደምሴ፡፡ 1997፡፡ *የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ መጽሀፍ አስረኛ ክፍል፡፡* አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ታሪኩ ፋንታዬ፡፡ 2001፡፡ አማርኛ ሁሉ ለሁሉ፡፡ አ.አ፣ ዜድ.ኤ ማተሚያ ቤት

አለም እሸቱ እና ግርማ አውግቸው፡፡1998፡፡የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ መጽሃፍ አስራ ሁለተኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፤ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

አምሳሉ አክሊሉ እና ዳኛቸው ወርቁ፡፡1993፡፡የአማርኛ ፈሊጦች፡፡ አ.አ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

አብክመ ፕላን ኮሚሽን፡፡ 2012 የስነ ህዝብና ልማት ቅንጅት ዳይሬክቶሬት፣ ያልታተመ፡፡

አብክመ ፡፡ የአካባቢ የደንና የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ባለስልጣን የኮሚኒኬሽ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት፣ ያልታተመ፡፡

አ.አ.ክ.አ. ት/ቢሮ፡፡ 2007፡፡ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛና ህገ ወጥ ዝውውርን ለመከላከል የተዘጋጀ መጽሃፈ ዕድ፣ ያልታተመ፡፡

ዘሪሁን አስፋው ፡፡1998፡፡ የስነጽሁፍ መሰረታውያን፡፡ አ.አ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የሺጥላ መንግስቴ ፡፡2004፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ መጽሀፍ አስራ አንደኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

የሻው ተሰማ ፡፡ 1996፡፡ ልሳነ ብዕር ከመ ልሳነ ሰብዕ፡፡ አ.አ ፣ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

__________፡፡ 1998፡፡ የተውኔት አጽናፍ መነጽር ፡፡አ.አ ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ድንቄሳ ደሬሳ እና ጽጌ አበበ፡፡ 1999፡፡የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ መጽሀፍ አስራ አንደኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡1989፡፡ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡ አ.አ ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጽጌሬዳ ጫንያለው ፡፡ አዲስ ዘመን፣ ነሀሴ 12 /2011፡፡

______________፡፡ አዲስ ዘመን፣ ሐምሌ 28/ 2011 ፡፡

# የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 1 | ፪ 2 | ፫ 3 | ፬ 4 | ፭ 5 | ፮ 6 | ፯ 7 | ፰ 8 | ፱ 9 | ፲ | 10 |
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | 100 |
| ፪፻ | 200 | ፫፻ | 300 | ፬፻ | 400 | ፭፻ | 500 | ፮፻ | 600 | |
| ፯፻ | 700 | ፰፻ | 800 | ፱፻ | 900 | ፲፻ | 1000 | ፳፻ | 2000 | |
| ፴፻ | 3000 | ፵፻ | 4000 | ፶፻ | 5000 | ፷፻ | 6000 | ፸፻ | 7000 | |
| ፹፻ | 8000 | ፺፻ | 9000 | ፻፻ | 10000 | | | | | |